# ማዕዶት



መስከረም ፲፱፻፹፱ ዓ ም
አዲስ አበባ

ቍጥር ፳፱

www.ethiopianorthodox.org

ቤ/ት ሊቃና ቤተክ/ሊ
የግዕ ቤተ መጻሕፍት

# ማዕዶት

መስከረም ፲፱፻፹፪ ዓ/ም
ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

# ማዕዶት

« ማዕዶት » የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ ከልሳነ ግእዝ ሲሆን ትርጓሜውም /መሸጋገሪያ ማለት ነው ፤ ይህ መጽሔት በዚህ በሽግግር ወቅት በተሐድሶ ላይ የምትገኘውን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነቷንና ሥርዓትዋን ወቅታዊ እንቅስቃሴዋን ፣ ዜናዋንና ታሪካዊ ልዕልናዋን ሁሉ የሚገልጽ ስለሆነ «ማዕዶት» ተብሎ ተሰየመ ።


ዋና አዘጋጅ

ሊ/ትጉሃን ገ/ክርስቶስ ኃ/ማርያም

የስልክ ቁጥር 110754

ፖ/ሣ/ ቁ/ 1283

መስከረም ፲፱፻፹፪ ዓ/ም

አዲስ አበባ


## ማውጫ


| ተራ ቁ/ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ | ፫ |
| ፪ | የቅዱስ ፓትርያርኩ ቃለ ምዕዳን | ፰ |
| ፫ | ፓትርያርኩ በውጭ ሀገር ያደረጉት | ፱ |
| ፬ | የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፩ኛ ዓመት | ፲፭ |
| ፭ | ቅዱስ ሩፋኤል | ፳ |
| ፮ | ቅዱስ ዮሐንስ | ፳፩ |
| ፯ | አቡነ አረጋዊ | ፳፫ |
| ፰ | የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅም | ፳፬ |
| ፱ | በቃሉ የሚያምን ይድናል | ፳፭ |
| ፲ | በብሪታንያ የኢትዮጵያ ቤ/ ክ/ የሥራ ፍሬ | ፳፰ |
| ፲፩ | ስብከተ ወንጌል በልማት ተግባር | ፴፩ |
| ፲፪ | የአቶ ኃይሉ መላኩ አጭር የሕይወት ታሪክ | ፴፬ |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፣

www.ethiopianorthodox.org

«ርዕሰ አንቀጽ»

# በሥራ ለሥራ መመረጥ

ሥራ ክቡር ነው በሁሉም ዘንድ የተወደደ ነው ፤ እግዚአብሔርም ዓለማትን ከመፍጠሩ በፊት በመላእክቱ አንደበት ሲመሰገን ፥ ሲወደስና ሲቀደስ የኖረና ለዘለዓለም የሚኖር ሲሆን በበለጠ እንዲመሰገንም ሥራን ሠርቶ አሳይቶአል ። ይኸውም ዓለማትን እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ አምጥቶ ከመፍጠሩም በላይ በዓለም ላይ የሚኖሩትን ፍጥረታት ሁሉ ከዕለተ እሁድ እስከዕለተ ዓርብ ድረስ ፈጥሮ ሥራውን ፈጽሞ በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ አረፈ ሲል ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል ።

ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ሰውን የዕለት ምግቡን የዓመት ልብሱን ለማግኘት ሠርቶ ወዝቶ ወጥቶ ወርዶ መኖር እንዳለበት ሲያስረዳ «ወደወጣህበት መሬት እስክትመለስ በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ» ብሎ አዞታል ።

በዚሁ መሠረታዊ የአምላክ ቃል ሥራን ሠርተው በማሳየታቸው ምክንያት ለአሠሪነት የተመረጡ በመልካም አሠሪነታቸውም ደግሞ ንዑዳን ክቡራን ተብለው በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ የተመሰገኑና የሚመሰገኑ ብዙ ናቸው ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ለሥራና ለአሠሪነት ከተመረጡ በኋላ ኃላፊነታቸውን በመዘንጋት ወደ ግል ጥቅማቸው በማዘንበል ስለራሳቸው ኑሮ መሳካት ብቻ ሲጠበቡ ወቅታዊ የሥራ ጊዜአቸውን በአልባሌ ነገረ ዘርቅ ያሳልፉ እንደነበሩ ከታሪክ ማኅደር ለመገንዘብ እንችላለን ።

ለምሳሌም ያህል እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ፥ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፥ እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ የመሳሰሉት የቤ/ክርስቲያን መሪዎች ለውዲቱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው ሌት ተቀን ሲሠሩ ስለክብርዋ ፥ ስለቅድስናዋና ስለዘለዓለማዊነትዋ በአላውያን ነገሥታት ፊት ሳያፍሩና ሳይፈሩ ሲመሰክሩላት ፥ ሲታሠሩላትና መከራንና ሥቃይንም ሲቀበሉላት እነአርዮስ ፥ እነንስጥሮስና እነ ሰባልዮስ ደግሞ ነገረ መለኮቱን እያጣመሙ በመተርጐም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ እንክርዳድ የሆነው የክህደት ትምህርታቸውን እየዘሩ ለማፍረስ በመሞከር መዋዕለ ዘመናቸውን በእርግማንና በውግዘት እየተባረሩ ጊዜያቸውን እንዳሳለፉ ታሪክ ነውና እኩይና መሰርይ ታሪካቸውን ከተቀደሰው የአባቶች ታሪክ ጎን ተዘግቦ ሲነበብና ሲነገር ይኖራል ።

ታሪክ የማያቋርጥ ሂደት እንደመሆኑ መጠን በየጊዜያቱና በየዘመናቱ የአባቶቻቸውን የተቀደሰ ሥራ ተከትለው እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን ከልጅነት እስከ ዕውቀት (ሲበት) በርትዕት ሃይማኖት ጸንተው አገልግለው በተቀደሰ ሥራቸው ከታሪክ ወደ ታሪክ እየተሸጋገሩ ለከፍተኛ የቅድስና ደረጃ የደረሱ ሠርተው ለማሠራት የበቁ ቅዱሳን አበው ጥንትም አሁንም አሉ ።

ከነዚህም ቅዱሳን አበው መካከል አንዱ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከሕጻንነት እስከ ዕውቀት አገልግለው ለከፍተኛና ለመጨረሻው የቤተ ክርስቲያን ማዕርግ የደረሱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ናቸው ብንል ከእውነት የራቅን አይደለንም ። ምክንያቱም ቅዱስ ፓትርያርካችን ከልጅነት እስከ ትምህርት ከምንኩስና እስከ ቁምስና ከጵጵስና እስከ ፓትርያርክና ድረስ ከደረጃ ወደደረጃ እየተሸጋገሩ የሠሩአቸውን የተቀደሱ ሥራዎቻቸው የመቅረዝ ብርሃን ሆነው ለትውልድ ሲያበሩ የሚኖሩ በመሆናቸው ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የማስተማር ፤ የሠርቶ ማሠራትና የአስተዳደር ችሎታቸውን ያስመሰከሩ መዓርገ ጵጵስና ከማግኘታቸው በፊትም ሆነ በኋላ በተሠማሩባቸው የሥራ ቦታዎች ነው ይኸውም ያረጁ አብያተ ክርስቲያናትን አሳድሰዋል የፈረሱና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትንም በብዛት አሳንጸዋል ። ለአገልጋይ ካህናት መኖሪያ ቤቶችን በማሠራት የአብነት መምህራን ቋሚ ደመወዝ ለተማሪዎቻቸውም የዕለት ጉርስና የዓመት ልብስ እንዲያገኙ አድርገዋል በየቀበሌውና በየወረዳው እየተገኙም ሥልጣነ ክህነትን በመስጠትና ሰበካ ጉባኤን በማጠናከር ኃላፊነታቸውን በተቀደሰ ተግባር ተወጥተዋል ።

በማኅበራዊ አገልግሎት በኩልም የተመለከትን እንደሆን ጥንታውያን የሆኑ ቅርሶቻችን እንዲጠበቁ ፤ ንዋያተ ቅድሳቶቻችን በብዛት እንዲመረቱ ፤ የእደ ጥበባት ድርጅቶችን በማቋቋም ከሀ/ስብከታቸው በተገኘው ገቢ የካህናት ማሠልጠኛ ማዕከል በማደራጀት መንፈሳዊ አዳሪ ት/ቤትን በመካፈት የሙት ልጆችን አሰባስበው በማሳደግ በድርቅ የተጎዱትን በዕለት ደራሽ ርዳታና በመልሶ ማቋ

www.ethiopianorthodox.org

ጳም ፣ በሚሊዮን የሚቈጠር ችግኝ የተራቆቱትን አካባቢዎች በማስተከልና በእንክብካቤ እንዲጠበቁ በማድረጋቸው ባሁኑ ጊዜ ዕፀዋቱ በጥሩ ሁኔታ አድገው ይታያሉ ።

በከብት ርባታ ፣ በውኃ ልማት ፣ በገጠር መንገድ ሥራና በልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች ባሳዩት ችሎታ በአገር አቀፍ ሲጐተመዝና በአንደኛነት ደረጃ ለአምስት ተከታታይ ዓመታት ሽልማት አግኝተዋል፤ቅዱስነታቸው የቤ/ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት በማክበርና በማስከበር ከሥራ ባልደረቦቻቸውም ጋር ከሚያሳዩት የአስተዳደር ችሎታ በላይ የአገሪቱን ሕግና ደንብ አክብረው የሚሠሩ ተወዳጅ አባት በመሆናቸው በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ብሔራዊ ሸንጎ ምርጫ በጐንደር ዙሪያ በአንድ የምርጫ ጣቢያ በዕጩነት ቀርበው ድምፅ ከሰጠው ፹፯ሺህ ፩፻፹፯ ሕዝብ መካከል ፲፯ሺህ ፱፻፶፱ ድምፅ በማግኘት ተመርጠው በሸንጎው ሕዝብን በማገልገል ላይ ያሉ አባት ናቸው ።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሥራ ከዚህ በላይ በተዘረዘረው ብቻ የሚካተት ሳይሆን በነበሩበት ሀ/ስብከታቸው በማኅደረ ማርያም የሐዲሳት የድጓና የቅዳሴ ት/ቤት አሠርተው ለመምህራን ከ፵ እስከ ፻፫ ብር ደመወዝ እንዲከፈላቸው ለየደቀ መዛሙርቶቻቸውም ድጎማ እንዲያገኙ አድርገዋል የጣና ቂርቆስን ገዳም በብር ፳ሺህ ፳፻፴፰ ብር አሳድሰዋል ለጣና ሬማ መድኃኔ ዓለም ቤ/ክርስቲያን ፬ሺ (አራት ሺህ ብር) ረድተዋል የደረሞ ቅ/ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ብር ፳፩ሺ፩፻፲፬ (ሃያ አንድ ሺህ አንድ መቶ አሥራ አራት ብር) በማውጣት ሙሉ ዕድሳት አድርገውለታል ።

እንዲሁም ጥንታዊው የገርቢ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በብር ፰ሺ፰፻፷ ብር(ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ብር)እንዲታደስ አድርገዋል ወደ አዘዞ ሰሚ ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናት ማሠልጠኛ የሚወስደው መንገድ በምግብ ለሥራ መርሐ ግብር እንዲሠራ አድርገዋል። በጐንደር መንበረ መንግሥት ጥበበ እድና የአዳሪ ቤቱ ዙሪያ ርዳታ በመጠየቅ ከ፱ሺህ (ዘጠኝ ሺህ ብር) በላይ በማውጣት እንዲሠራ አድርገዋል ። በጐንደር ጉባኤ ቤትና የዶክተር አባ አየለ ዓለሙን የመቃብር ቤት የአራቱን ጉባኤያት ት/ቤት ሥዕል እንዲሠራበት አድርገዋል ።

በሊቦ አውራጃ በቆላ እብናት ለአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር ብር ፲፩ ሺህ ረድተዋል ፤ በጐንደር ከተማ በአዘዞ አባ ሳሙኤል በመጠለያ ጣቢያ ለሚረዱ ከልማትና ከክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ጋር በመተባበር የኤሌክትሪክ ምጣድ ርዳታ አድርገዋል በዳባት ወረዳ የሚገኘውን የደፍቂ ቅ/ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን በብር ፭ሺህ (አምስት ሺህ ብር) አሳድሰዋል ለአምስት ገዳም ብር ፬ሺ (አራት ሺህ ብር) ሰጥተዋል ።

ለጣርከ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፯ሺህ (ሰባት ሺህ ብር) ረድተዋል ፤ ዐደባባይ ኢየሱስን በብር ፵ሺ ብር (አርባ ሺህ ብር) አሳድሰዋል የድምፅ ማጉያ አስገብተዋል፤በጐንደር ዙሪያ አውራጃ ለሚገኘው ለቸንከር ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ብር ፮፻፷፬ሺ ብር (ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ብር ርዳታ ጠይቀው ብር ፴፬ሺ ብር (ሠላሳ አራት ሺህ ብር) ተሠርቶበታል ቀሪውም በየጊዜያቱ ይቀጥላል ከማክሰኝት እስከ አርባ ለመንገድ ሥራ ብር ፴ሺ ብር (ሠላሳ ሺህ ብር) ርዳታ እንዲያገኝ አድርገዋል ከዕብናት እስከ ጎሐላ ለመንገድ ሥራ ብር ፮ሺ ብር (ስድስት ሽህ ብር) ርዳታ አስገኝተውለታል ።

በሰሜን አውራጃ ለሚገኙት ጥንታውያን ገዳማት ለዋልድባ አባ ሚናስ ገዳም ከ፲ ሺህ ብር በላይ ለአባ ጣዕመ ክርስቶስ ገዳም ከብር ፲ሺህ ብር በላይ፣ለሰቋር ዋልድባ ብር ፬ሺህ ግምት ያላቸው ቁሳቁስ በጎርጎራ ገዳም በደሴተ ጣና ለሚገኙ ገዳማት ለማን እንዳባ ገዳም ብር ፩ሺ፰፻፹ (ብር አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ) ለብርጊዳ ማርያም ገዳም ብር ፩ሺህ ብር (አንድ ሺህ ብር) ለበሬ መግዣ ሰጥተዋል

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ርዳታ በመጠየቅ አቅም በፈቀደ መጠን በተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት የቆዳ የሽመና ፣ የሹራብ ሥራ ፣ የልብስ ስፌት ፣ የወፍጮና የዳቦ ማሽን እንዲቋቋም አድርገዋል ፤ በተጨማሪም ለስብከተ ወንጌል ፣ ለሰንበት ት/ቤትና ለሕዝብ መሰብሰቢያ የሚያገለግሉ አዳራሾች በየአብያተ ክርስቲያናቱ አካባቢ በብዛት አሠርተዋል ። ሕዝቡ ንጹሕ ውሃ ማግኘት እንዲችልም የውኃ ጉድጓድ በማስቆፈር ለዚሁ የሚያገለግል ሞተርና ቧንቧ ሰጥተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለፓትርያርክነት ውድድር ከቀረቡት ሁለት አበው ሊቃነ ጳጳሳት ሦስተኛ ሲሆኑ በዲሞክራሲያዊ አመራረጥ ቅዱስነታቸው በከፍተኛ ድምፅ በማለፋቸው ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም በመንበረ ጸባኦት ቅ/ሥላሴ ካቴድራል የፓትርያርክነት ማዕርግ ተቀዳጅተዋል ።

በበዓለ ሢመተ ፓትርያርኩ ዕለት የመንግሥት ተወካዮች ፣ የአኀት አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞች ማለትም የአርመን ፣ የሕንድ ፣ የራሽያ ፣ የግሪክ በተለይም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ተወካይ ፣ አምባሳደሮች ፣ ኮር ዲፕሎማቲኮች ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ፣ የደብር አለቆችና ሊቃውንት ፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና በብዙ ሺህ የሚቈጠር የአ- አበባ ሕዝበ ክርስቲያን ተገኝተዋል ።

በዓሉ ወደር የማይገኝለትና ካሁን በፊትም ይህን የመሰለ በዓለ ሢመተ ፓትርያርክ ያልታየ እንደነበር የዓይን ምስክሮች ይናገራሉ ።

ቅዱስ ፓትርያርኩም ይህንኑ የደመቀ በዓል በማስመልከት ባደረጉት አጠቃላይ ንግግር «----

የእኅት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወኪሎች በዚህ የቤ/ክርስቲያናችን በዓል ላይ በመገኘታችሁ የነበረውንና ያለውን ግንኙነታችን በበለጠ እንደሚያጠናክረው እየተማመንን ጥሪያችንን አክብራችሁ የመጣችሁ ክቡራን አምባሳደሮች ኮርዲፕሎማቲኮችና በአጠቃላይ በዚህ በዓለ ሢመተ ፓትርያርክ ዕለት የተገኛችሁ ሁሉ በቤተ ክርስቲያናችን ስም ምስጋናችንን እናቀርባለን »ብለዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ አባታዊ ቃለ ምዕዳናቸውን በማራዘም ሲናገሩ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንትም አሁንም ሰፊ የሥራ መስክ አላት ፤ ይህ ሥራም በጥራትና በብቃት ለመወጣት ይቻል ዘንድ ሁሉም ከምን ጊዜውም በበለጠ ለሥራ እንዲሰለፍ ይገባል» በማለት አስገንዝበዋል ።

ስለዚህ « ለሁሉም ጊዜ አለው» እንደተባለው ሥራ ሠሪውንና አሠሪውን ባገኘ ጊዜ በጅምርና

በዕቅድ የነበረውን ሁሉ ከፍጻሜ እንደሚደርስ የታመነ ስለሆነ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሠርቶ የማሳየትና ትጉሃን ሠራተኞችንም አሠርቶ ለቤተ ክርስቲያን በረከትና ረድኤት የማስገኘት ልዩ ስጦታቸው በመሆኑ ርእሰ ቤተ ክርስቲያን ሆነው ከተመረጡ ወዲህ እንኳ በአንድ ዓመት ውስጥ ባሳዩት የሥራ ውጤት አስመስክረዋል ። ለወደፊትም የቅዱስ ፓትርያርኩ መዋዕለ ሢመት ለቤ/ክርስቲያናችን እጥፍ ድርብ በረከት የሚያጎናጽፍ መሆኑን በማመን እግዚአብሔር ለቅ/ ፓትርያርኩ ረጅም ዕድሜና ጤና እንዲሰጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ትጸልያለች ።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
የ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ዘመነ መለወጫ ምክንያት በማድረግ ለመላ የኢትዮጵያ ምእመናን
በራዲዮ ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጦች ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ።

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ፤

— በገጠርና በከተማ ያላችሁ ምእመናን

— የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር ነፃነትዋንና አንድነትዋን ለመጠበቅ በጠረፍና በመሐል ሀገር በየብስና በባሕር በሥራ ላይ የምትገኙ ሠራዊት

— በሕማም ምክንያት በየሐኪም ቤቱ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ፤ ከዘመናት በፊት የነበረ ፣ በዘመናት መካከል ያለና ዘመናትን አሳልፎ የሚኖር ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ በሰላም አሸጋገራችሁ ።

«ወይእዜኒ ባርክዎ ለእግዚአብሔር አምላከ ኵሉ ዘይገብር ዐቢየ በኵሉሂ ወያነሥኦ መዋዕሊነ ወይገብር ምስሌነ በከመ ምሕረቱ የሀበነ ትፍሥሕተ ልብ ፣ ወይገብር ሰላመ በመዋዕሊነ» የልብ ደስታን እንዲሰጠን በዘመናችን ሰላምን እንዲያደርግልን ፣ በሁሉ ዘንድ ታላቅ ሥራ የሚሠራ ሠሪ ዘመን፣ ረዥምም ዕድሜ የሚሰጥ ለእኛ እንደ ቸርነቱ የሚሠራ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔርን እነሆ ዛሬ አመስግኑ (ሲራክ ፶፥፳፫) እግዚአብሔር አምላካችን በፈጣሪነቱ ፣ በመግቦቱና በከሃሊነቱ በየዘመናቱም ለሰው ልጆች በሚሠራው አዳዲስ ሥራ ሁል ጊዜ በአዲስ ምስጋና ሲመሰገን ይኖራል ።

ሰዓትን በዕለት ፣ ዕለትን ፣ በወር ወርን በዓመት ፣ የወሰነና ፍጥረትን ሁሉ በቃሉ ያከናወነ ፣ ይኸንም የሥነ ፍጥረቱን ከንውን ለሰው ልጆች የገለጸ እግዚአብሔር በመሆኑ ዛሬ ባለፈውም ሆነ ነገ በምንጀምረው ዓዲስ ዓመት ሊመሰገን ይገባዋል ። ዝናሙን በወቅቱ በማዝነሙ የተዘራውን በማብቀሉ ምድርን በአበባና በፍሬ በማስጌጡ በየወቅቱ የሥነ ፍጥረት ሂደት ሳይፋለስ እንዲኖር በማድረጉ በዚህም፣ ከሃሊነቱንና ጌትነቱን በማሳወቁ ምስጋናው ሳይቋረጥ ይኖራል ።

በዓመቱ ውስጥ እግዚአብሔር ሥራ ያልሠራበት ፣ የማይሠራበት ጊዜ ባለመኖሩ ያለፈውም የሚቀጥለውም ዓመት የእግዚአብሔር ዓመት ይባላል ። ፍጡር ለተወሰነ ዘመን ኖሮ የተወሰነ ሥራ ሠርቶ ያልፋል እግዚአብሔር ግን ላለፈውም ለሚመጣውም ትውልድ በየዘመኑ ፣ ጌትነቱንና ቸርነቱን የሚገልጥ ሥራ ሲሠራ ይኖራል እንጂ በጌትነቱ በሥልጣኑ ሀልፈትና ውላጤ ሽረትም የለበትም እግዚአብሔር በቦታ እንደማይወሰን በጊዜም አይወሰንም ያልነበረበትና የማይኖርበት ጊዜ የለም ስለዚህም ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ይላል «አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም (መዝ ፻፩ ፡ ፳፯)

የተወደዳችሁ ምእመናን ፣

በነገው ዕለት ዘመን አልፎ አዲስ ዘመን ስለተተካ አዲስ ዘመን ስለተለወጠ እርስ በርሳችን ደስታችንን እንገልጣለን እንኳን አደረሳችሁ በመባባልም የመልካም ምኞት ሰላምታ እንለዋወጣለን ።

ይህ በመሠረቱ አስፈላጊ ነው ፣ ሊደረግም የሚገባው ነው ። እንኳን ዘመን ሲለወጥ ሌሊቱ አልፎ ቀኑ ሲተካ የመልካም ምኞት ሰላምታ እንለዋወጣለንና ። ነገር ግን ዘመኑ በዘመን እንዲተካ በጥላቻ ፋንታ ሰላምንና ዕርቅን በመለያየት ፋንታ አንድነትን በኃጢአት ፋንታ ጽድቅን መተካት ያስፈልጋል ዓመቱ በዓመት እንደተለወጠ ስንፍናን በትጋት ድንቁርናን በትምህርት ክፋትን በበጎነት መለወጥ ይገባል ። እግዚአብሔር ዘመናትን አብዝቶ ወራትን አስፍቶ መስጠቱ መልካም ሥራ በመሥራት የተቸገሩትን እንድንረዳ ያዘኑትን እንድናጽናና ከክፉ ሥራችን እንድንመለስ በንስሐም እንድንታደስ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የዳዊትን ቃል መሠረት በማድረግ እንዲህ ይላል መልካም ዘመንን ሊያይ የሚፈልግ ሰው አንደበቱን ከክፉ ከንፈሮችንም ተንኰልን ከመናገር ይከልከል ከክፉ ፈቀቅ ይበል መልካምንም ያድርግ ሰላምን ይሻ ሰላምን ይከተል (፩ጴጥ ፫ ፡ ፲—፲፩) ዘመኑ አዲስና መልካም ዘመን የሚሆነው የሰው ልጅ እርስ በርስ መለያየትን ፣ ጠብና ጥላቻን ሽብርን ዛቻን አስወግዶ ጦርነትን አጥፍቶ ሰላምን ሲመሠርት ነው ። ሰላም ከሌለ ዘመኑ ዘመነ ፍዳ ፣ ዘመነ ኵነኔ ይሆናል ። ስለዚህ የማያቋርጥ ሰላም የማይደፈርስ ፀጥታ ፣ ለተወሰነ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በሁሉም አቅጣጫ ዘላቂ ሰላም እንዲኖር ሁሉም መተባበር ያስፈልገዋል ። ቤተ ክርስቲያናችንም ይህ ዓይነቱ ሰላም በሀገራችንና በመላው ዓለም ሁሉ እንዲሰፍን ዘወትር ትጸልያለች ።

በዓለም ላይ ጦርነት ጠፍቶ ሰላም እንዲሰፍን ፣ ሽብርና ሁከት ተወግዶ ፀጥታና ያለፍርኀት መኖር እንዲተካ ከፍተኛ ጥረትየሚያደርጉ የመንግሥታት መሪዎች ሁሉ በእግዚአብሔርም በሰዎችም ዘንድ ምስጋና አላቸው ። «ብፁዓን ገባርያነ ሰላም ፡— ሰላምን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው» ተብሎአልና (ማቴ ፭ ፡ ፱)

የነገውን የዘመን መለወጫ በዓል በደስታ ስናከብር ልንዘነጋው የማይገባን ጉዳይ አለ ። በዓለም ውስጥ ትክክለኛ ፍትሕና መብት እኩልነትና ነፃነት ፣ አጥተው የሚሰቃዩትን ወገኖች ሁሉ ማሰብ ይገባናል በረኀብ በእርዛትና በልዩ ልዩ ሕማም ምክንያት ተይዘው የሚጨነቁ ይኖራሉ እንዲሁም በመላው ዓለም በውሃ መጥለቅለቅና በመሬት መናወጥ በሌላም በተለያዩ ችግሮች ከቤታቸውና ከሀገራቸው የወጡ ፣ ንብረታቸውን ያጡ ወገኖች እጅግ ብዙዎች ናቸው ።

ስለዚህ ለእነዚህ ሁሉ በጉልበትም በሀብትም በዕውቀትም በሌላም አቅም በፈቀደው ሁሉ መርዳት ተገቢ ነው ።

ከዚህ ሁሉ ጋር ሁሉንም ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር በቸርነቱ እንዲአስባቸውና የቸርነቱን ሥራ እንዲአደርግላቸው ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ትለምናለች በዓልን የማክበር ትርጉሙ ይህ ነው ።

እግዚአብሔር ዘመኑን ዘመነ ሰላም ያድርግልን ። ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ሰላሙን ረድኤቱንና በረከቱን ለመላው ዓለምም አንድነትንና ፍቅርን ይስጥልን ።

አ ሜ ን



# ፓትርያርኩ በውጭ አገር ያደረጉት የሥራ ጉብኝት ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትሮያርክ ርእሰ ሊቀነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው በተለያዩ አገሮች ያደረጉትን የሥራ ጉብኝት ፈጽመው ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም አዲስ አበባ ሲገቡ ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከክብር ተከታዮቻቸው ጋርሚያዝያ፳፬ቀን፲፱፻፹፩ዓ ም ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ከአዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ተነሥተው ወደ ፍራንክፈርት ከተማ ጉዞአቸውን ቀጥለው ሚያዝያ ፳፭ቀን ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ላይ እንደደረሱ በምዕራብ ጀርመን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ከዚያም ጉዞው ወደ ጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ቀጥሎ ስለ ቤተ ክርስቲያንዋ የሥራ ይዞታና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ለቅዱስነታቸውና ለተከታዮቻቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ ባለ ሥልጣኖች ገለጻ ተደርጓል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ሆነው ሚያዝያ ፳፭ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ከጥዋቱ ፬.፴ ላይ ሽቱ ትጋርት አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የዲያኩንሺ ድርጅት ፕሬዚዳንት ቶረር ካርል ሔንስኒውካምና የዳቦለዓለም ድርጅት ተወካይ ዶ/ር ማይ እንዲሁም በሉንግራሺበኮለን፣ ከተማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ቀሲስ ዶክተር መርዓዊ ተበጀ ከጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ጋር በመሆን ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም በፍትሊንገን ከተማ በሚገኘው ታዋቂና ጥንታዊ የሜሪያን ካቴድራል ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ለጉብኝት ሲደርሱ የፎትሌንግን ሰበካ ጉባኤ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ለብ የሹት ትጋርት ሰበካ ጉባኤ ጳጳስ ሩብል ሌሎችም የቤተ ክርስቲያኑዋ ባለ ሥልጣኖች አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ፓትርያርኩ በሥፍራው ለተሰበሰቡት ምእመናን ቡራኬ ከሰጡ በኋላ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነትና ስለአላት ከፍተኛ ታሪካዊ ቅርስ ትምህርታዊ መግለጫ ሰጥተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በዚሁ ዕለት ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ከሽቱ ትጋርት ጉዞ ወደ ሀኖበር ከተማ ተደርጎ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የአፍሪካ ክፍል ጸሐፊ የቤተ ክርስቲያንዋ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ደማቅ አቀባበል ከአደረጉላቸው በኋላ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ከጧቱ ሁለት ሰዓት ተኩል መርከት በሚባለው ጥንታዊና ታዋቂ ካቴድራል እንደ ተገኙ ቄስ ገበዙ ካቴድራሉ በ፲፪ኛው ክፍለ ዘመን የተሠራ መሆኑን አስረድተዋል ።

በዚሁ ዕለት ከቀኑ ፬.፴ ላይ የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንን ለመጎብኘት ከሥፍራው ሲደርሱ የቤተ ክርስቲያኑዋ ምክር ቤት ሊቀ መንበር ብፁዕ ዶክተር ማርቲን ክሩስ ከሌሎች የቤተ ክርስቲያኗ ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን ደማቅ አቀባበል ከአደረጉ በኋላ ባደረጉት ንግግር ጥንታዊ ታሪክ ያላትን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ መቀበልና ግንኙነት መፍጠር በመቻላቸው ከፍተኛ ግምት እንደሚሰጡት አስረድተው በተከታታይ በኢትዮጵያ የደረሰው ድርቅና ያስከተለው ችግር የሚያሳስባቸው መሆኑንና ችግሩን ለማቃለል ትብብራቸው እንደሚቀጥል ስለኢትዮጵያና ስለቤተ ክርስቲያኗ ቅዱስነታቸው ትክክለኛውን እንዲገልጹላቸው ጥያቄ አቅርበዋል ። ከዚህ በኋላ ከቅዱስነታቸውና ከተከታዮቻቸው ጋር ውይይት ተደርጎ ቅዱስነታቸው በሰጡት መግለጫ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ፻፷፭ሺ የሚበልጡ ፣ ካህናት ከ፴ ሚሊዮን የማያንሱ ምእመናን ከ፳፱ የሚበልጡ አህጉረ ስብከት ፳፭ሺ ህ የሚሆኑ የሰበካ ጉባኤያት ከ፳ሺህ በላይ የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ፣ ፲ሺህ የሰንበት ት/ቤቶች ያሏት መሆኗን አስረድተው ቤተ ክርስቲያኗ ለምታካሂደው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት መንግሥት



www.ethiopianorthodox.org



ቅዱስ ፓትርያርኩ ቤተ ልሔም ጌታ የተወለደበትን ሲጎበኙ ፤

ለካህናት ደመወዝና ለሥራ ማስ ከያጃ በጀት በመመደብ ጥንታ ውያን አብያተ ክርስቲያናትንና ታ ሪካዊ ቅርሶችን በመንከባከብ ከፍ ተኛ ድጋፍ የሚሰጥ መሆኑን ገል ጸዋል ።

ብተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ዘመናዊ መልክ ለማ ስልጠን በተለያዩ የአስተዳደር አካ ባቢዎች የካህናት ማሠልጠኛ ተቋ ሞች እንዳሉ ገልጸው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማይምነት ነፃ በመውጣቱ ምእመናን መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ይሳተፋሉ ።

ቅዳሴም በግዕዝ ብሔራዊ ቋንቋ በአማርኛ እንዲካሔድ በመደ ረጉ ሕዝቡ መንፈሳዊ ፍላጎቱን ለማርካት ችሏል ።

ቅዱስነታቸው ከጀርመን ቤተ ክርስቲያን ለወደፊቱ ስለሚኖረው ግንኙነት በሴጡት ማብራሪያ እና ትና አባት የሌላቸውን ሕጻናት በመንከባከብ ፤ የካህናት ማሠል ጠኛ ተቋሞችን በማጠናከርና ለል ማት ፕሮጀክቶች ድጋፍ በመስጠት ከአሁኑ የበለጠ ትብብር ቢደረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፍላጎት መሆኑን አስረድተዋል ።

በዱዩስበርግ በተደረገው ጉብ ኝትም ከኪንደርኖት ሂልፈ የድ ርጅቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀ መንበር ዶክተር ሃንስ ፒተርዮልዮ ሲንግና ሚስተር ሉዳር ሉሲስ የኪ ንደር ኖት ሂልፈ የውጭ ጉዳይ ዳ ሬክተር ከሌሎችም ባለ ሥልጣኖች ጋር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆ ሬዎስ ሰፋ ያለ ውይይት አድርገ ዋል ።

ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ከ፱ ሰዓት ጀምሮ ከኪንደርኖት ሂልፈ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ውይይት በርከት ያሉ ጥያቄዎች ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ታሪክ ሕፃናትን ለመርዳት ቤተ ክርስቲ ያን ስለምታደርገው ጥረትና የመ ሳሰሉት ጥያቄዎች ቀርበው የጀር መን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ባደረገችው ጥሪ መሠረት ቅዱስ ነታቸውና ተከታዮቻቸው የተለያዩ የሃይማኖት የርዳታ ሰጭ ድርጅ ቶችን ጉብኝተው ከኃላፊዎች ጋርም ተነጋግረው ከመልካም ውጤት ላይ በመድረሳቸው እንዲሁም እስከ አሁን ለቤተ ክርስቲያናችን ስለ ተደረገው ርዳታ ምስጋና እናቀር ባለን ብለዋል ።

የወንጌላዊት የልማት ትብብር ማኅበር ኢ. ዘ. ድ. ኢ. ፓ. ዳያስንያ ዳቦ ለዓለም ኪንደርኖት ሂልፈና የመሳሰሉት ድርጅቶች በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቻችን ያደረጉት ድጋፍ የሚያስመሰግን በመሆኑ ወ ደፊትም ጉዳት የደረሰባቸውን መ ልሶ ለማቋቋምና በልማት ለማሠ ማራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእኅት አብ ያተ ክርስቲያናትን ተጨማሪ ድ ጋፍ የምትሻ መሆኑን አስረድተ ዋል ።

ቅዱስነታቸው ስለ ኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊትነትና ታሪካዊነት በሰ ጡት መግለጫ ቤተ ክርስቲ ኗ ጥንታዊና ታሪካዊ ቅርስ ያላት ለሕ ዝቦች ድኅንነት፣ነጻነትና እኩልነት በአጠቃላይ ለዓለም ሰላም በም ታደርገው ጥረት በአፍሪካ አህጉ ርና በዓለም ሁሉ ዝናን እንዳተረ ፈች በሰፊው አብራርተዋል ።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ አማካ ይነት በኮረም መጠለያ ጣቢያ ሰበ ታ በሚገኘው የሕፃናት ማሳደጊያ በመሳሰሉት እናት አባቶቻቸው የ ሞቱባቸው ከ፲ሺህ የማያንሱ ሕፃ ናት የሚረዱ መሆኑ ተገልጾ በዚሁ ዕለት ከቀኑ ፲ ሰዓት ላይ የኪንደ ርኖት ሂልፈ የዳይሬክተሮችና የድ ርጅት የበላይ ጠባቂ ቦርድ አባ ላት በተገኙበት ውይይት ተደርጎ የማስታወሻ ስጦታ ተለዋውጠዋል

ቅዱስነታቸው ከዱዩስበርግ ወደ ኮለን ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ተጉዘው ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ሉንግሪብ በሚባል ቦታ በጀ ርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲ ያን ትብብር በተሰጠ በቅዱስ ሚካ ኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዳግም ትንሣኤን በግል አክብረዋል ።

ሥርዓተ ቅዳሴውም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ሥርዓት የተከናወነ ሲሆን በዚሁ ወቅት አንድ ኢትዮጵያዊ ክርስትና ተነሥቶ ተጠምቆአል ።



ቅዱስነታቸው በቤተ ክርስቲያኑ ለተሰበሰቡት ምእመናን ሰፋ ያለ ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተው ከቅ ዳሴው ሥርዓት ፍጻሜ በኋላ እንግ ዶችን ተቀብለው አነጋግረዋል ።

በዚሁ ሥነ ሥርዓት ላይ የሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ሊቀ ጳጳስ ንግግር አድርገ ዋል ።

ፕሮፌሰር ሃየር የጀርመን ወንጌ ላዊት ቤተ ክርስቲያን ሱፐር እን ቴንዳንት ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚ ያደርጉት ጥናትና ምርምር ስለሚ ሰጡትም ያልተቋረጠ ድጋፍ ቅዱ ስነታቸው በማድነቅ ምስጋና አቅ ርበውላቸዋል ።

እንዲሁም ዶ/ር ቄስ መርዓዊ ተበጀ የቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲ ያን አስተዳዳሪ እንኳን ደህና መጡ በማለት ጀምረው በአደረጉትም ንግ ግር በጀርመን የተመሠረተው የቅ ዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በቅ ዱስነታቸው በመባረክ ከፍተኛ ዕድል መሆኑን አብሥረው ቤተ ክርስቲያኑ ለምእመናን ስለሚሰጠ ው መንፈሳዊ አገልግሎት ገለጻ አድርገዋል ።

በመጨረሻም ፕሮፌሰር ሃየር ባደረጉት ንግግር በኢትዮጵያ በመ ካሔድ ላይ ያለው የመሠረተ ትም ህርት ዘመቻ ምእመናን ወንጌልን ለማንበብና ለመረዳት አመቺ መሆ ኑን አስረድተው የኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎ



ቅዱስነታቸው ከቤተ ልሔም ከንቲባ ጋር በቤተ ልሔም ጉብኝት ሲያደርጉ ፤



www.ethiopianorthodox.org



ፓትርያርኩ በግሪክ ርእስ ከተማ ተገኝተው ት/ቤቶችን ሲጐበኙ ፣

ት በኩል ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ እንደምትገኝ አስረድተው ይህንኑ አገልግሎት ለማጠናከርና ጥንታዊ የሆኑ መንፈሳዊ ቅርሶችን ለመንከባከብ የሚችሉ ካህናትን ለማሠልጠን ታቦር ሶሳይቲ ድርጅት ተቋቁሞ አበረታች ውጤት እያሳየ መሆኑን አስረድተዋል ።

ቅዱስነታቸውም ፕሮፌሰር ሃየር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ፍቅርና ከፍተኛ ድጋፍ አውስተው በድጋሚ አመስግነዋቸዋል ።

በፕሮግራሙ ማጠቃለያ በውበቱና በጥንታዊነቱ የታወቀውን የቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል በቅዱስነታቸውና በተከታዮቻቸው ተጎብኝቶ እንዳበቃ ወደቦን ከተማ አምርተዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ከተከታዮቻቸው ጋር ሚያዝያ ፴ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ከጧቱ ፬-፴ ቦን ሲደርሱ የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የርዳታ ማዕከል ኢ-ዜ-ዶ ኦ ዳይሬክተር የሚስተር ባወር ም ሚኒስትር ማንስክ ሚስተር በርገር የድርጅቱ የአፍሪካ ጉዳይ ኃላፊና የድርጅቱ አባላት ለቅዱስነታቸው ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

ከአቀባበሉ ሥርዓት በኋላ በተደረገው የጋራ ውይይት (ኢ-ዜ-ዶ- ኢ) ለኢትዮጵያ ርዳታ በመስጠት ላይ መሆኑን ገልጸው ይኸው ርዳታ ወደፊትም እንደሚቀጥል የድርጅቱ ም/ ዳይሬክተር አስረድተዋል ።

ርዳታው በኢትዮጵያ በኩል በሥራ ላይ የሚውለው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመካነ ኢየሱስ የመልሶ ማቋቋም የልማት ማኅበር (ኦ-ር-ዲ-ኤ) በቃለ ሕይወት አማካይነት መሆኑ ተገልጾአል ።

ከዚያም በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ባለው የደን ልማት ሁለተኛ ዙር ርዳታ የ፳፫፻፫ ሺህ ዶች ማርክ ሰነድ(በኢ-ዚ-ድ) ድርጅትና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኩል ብፁዕ ዶክተር አቡነ ገሪማ ፈርመዋል በዚሁ ወቅት የመንግሥት ባለሥልጣኖች የሃይማኖት መሪዎች ተገኝተው እንኳን ደኅና መጡ በማለት ንግግር አድርገዋል ።

ፓትርያርኩ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፹፭ ዓ/ም ከጧቱ ሁለት ሰዓት ከቦን ወደ ቤንስሔይንስ ከተከታዮቻቸው ጋር ሆነው በደረሱበት ወቅት የክርስቶፎል ዕውራን ሚሲዮን ም ዳይሬክተርና የሚሲዮኑ የምሥራቅ አፍሪካ የድስክ ኃላፊ ከሠራተኞቻቸው ጋር ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል



በዚህ ጊዜ ም/ዳይሬክተሩ ቅዱስነታቸውን እንኳን ደህና መጡ በማለት ባደረጉት ንግግር ለ፳ዓመታት በኪንደርኖት ሄልፈ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ የሠሩ መሆናቸውን ከአስረዱ በኋላ ድርጅቱ የሚረዳቸውንና ያደረገውን እርዳታ ገልጸው ወደፊት በኢትዮጵያ ለሚገኙ ተመሳሳይ ችግረኞች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ (ዲ- ካ-ድ-) አማካይነት ርዳታ እንደሚያደርግአውስተዋል።

ቅዱስነታቸው በውይይቱ መጨረሻ ላይ በሰጡት መግለጫ በጋብቻና በእምነት መካከል በሚኖረው ልዩነት በዓለም ዙሪያ ያሉ ክርስቲያኖችን ከፍተኛ ችግር እንደሚገጥማቸው ገልጸው በጋብቻና በእምነት አንድ መሆን ለክርስትና ሕይወት ጠንካራ መሠረት መሆኑን አስረድተዋል ።

ከዚያም በማያያዝ ስለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት አባል መሥራች አባል በመሆኗ የምክር ቤቱን ውሳኔዎች እንደምታከብርና ለዓለም ሰላምና ለሰው ልጆች እኩልነት እንደምትቆም ገልጸው በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል ግንኙነት እንዲፈጠር ቤተ ክርስቲያናቸው የበኩሏን ጥረት እንደምታደርግ አስረድተዋል ።

ቅዱስነታቸው ግንቦት ፪ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ከጧቱ አንድ ሰዓት ላይ ታቦር ሶሳይቲ በሚሰበሰብበት በሃይድልበርግ ዩኒቨርስቲ በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ጉብኝት አድርገዋል ።

በዚሁ ጉብኝት ጊዜ ቅዱስነታቸው በአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ ቃለ ምዕዳን ሰጥተው ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነት ገለጻ አድርገዋል ።

ከጧቱ ፪ሰዓት ከሠላሳ በሃይድል በርግ ዩኒቨርስቲ የቲዎሎጂ ፋኩሊቲ ቅዱስነታቸው እንደደረሱ የፋኩልቲው ዲን ከሌሎች ሠራተኞች ጋር በመሆን ደማቅ አቀባበል ከአደረጉላቸው በኋላ በሰጡት መግለጫ ኢትዮጵያውያን ካህናት በፕሮፌሰር ሃየር ተባባሪነት በዩኒቨርሲቲው ለመማር መብቃታቸውንና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መምህራንና ደቀ መዛሙርት የሚያደርጉት ትብብርና ርዳታ አስአረድተዋል ።

ቅዱስነታቸው ንግግሩን ከአዳመጡ በኋላ ለፕሮፌሰር ሃየርና ለታቦር ሶሳይቲ አባላት የማስታወሻ ስጦታ የሰጡ ሲሆን ስለሚያደርጉት ጥረት ምስጋና አቅርበውላቸዋል ።

ግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ከሃይደል በርግ ጀኔባ የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው በአውሮፕላን ጣቢያ እንደደረሱ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ም/ዋና ጸሐፊ ዶክተር ሲበሸኛ አቶ መልአኩ ክፍሌ በስደተኞች ክፍል ኃላፊ የምክር ቤቱ ኃላፊ



ብፁዕ ወቅዱስ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ጉብኝት ሲያደርጉ ፣

www.ethiopianorthodox.org

ዎችና ሠራተኞች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከሰዓት በኋላ ጥን ታዊነት ያለውን የቅዱስ ጴጥሮስ ን ካቴድራል ለመጎብኘት ከሥፍ ራው ሲደርሱ « ኢትዮጵያ እጆ ቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘ ረጋለች » የሚለውን መዝሙር ካህናቱ እየዘመሩ ተቀብለዋቸዋል ።

በዚሁ ዕለት በምቤቲ ሲካኖስ ከሚባለው ድርጅት ኃላፊዎች ጋር ውይይት የተካሔደ ሲሆን በው ይይቱ ወቅት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲን ከል ማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መም ሪያ (ዲ - ካ - ድ -) ጋር የሠመረ ግንኙነት እንዳለ የተገለጸ ሲሆን ርዳታን በሚመለከት ከአሁን ቀደም ለተደረገውም ሆነ ለወደፊት ሊደ ረግ ስለሚገባው ብፁዕ አቡነ ገሪማ በሰፊው ገልጸዋል ።

በጀኔባ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቅዱስነታቸውና ተከታዮቻቸው በ መካከላቸው በመገኘታቸው በአቶ መልአኩ ክፍሌ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት የስደተ ኞች ጉዳይ ኃላፊአማካይነት የተሰማ ቸውን ደስታ ከገለጹ በኋላ ቅዱስነ ታቸው በአሰሙት መንፈሳዊ መል እክትና በሰጡት ቃለ ቡራኬ «ወላ ጆች ሕፃናትን ከሀገራቸው ባህልና ታሪክ ጋር ተዋውቀው እንዲያድጉ ገልጸው ስለ ሀገር አንድነትና ነፃ ነት መቆርቆር አስፈላጊ መሆኑን አስረድተዋል ።

በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋምላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢ መሆኑን አስረድተው አገ ልጋይ ካህናት የሚመደብላቸው መሆኑን ስለገለጹላቸው ምእመናን ከፍተኛ ደስታ ተሰምቷቸዋል ።

ቅዱስነታቸው በእስራኤል ሀገር

ያደረጉት ሐዋርያዊ ጉብኝት ፣

ቅዱስ ፓትርያርኩ የክብር ተከታ ዮቻቸውን አስከትለው ግንቦች ፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም በ፰ ሰዓት ቴል አቢብ አውሮፕላን ጣቢያ ሲደርሱ



ቅዱስነታቸው በቦሌ አውሮፕላን የእንግዶች መቀበያ ሳሎን ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጡ ፣

ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ፣

ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የኢየ ሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ሌሎችም የገ ዳሙ መነኮሳትና ሠራተኞች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬ ዎስ ግንቦት ፺ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ከጣቱ ፲፪ ሰዓት ላይ ኢየሩሳሌም በምትገኘው የኢትዮጵያ ይዞታ በሆ ነችው ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ያስቀ ደሱ ሲሆን በዚሁ ዕለት ኢትዮጵ ያውያን ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክ ሊል ፈጽመዋል ።

ቅዱስነታቸው ከእሥራኤል መን ግሥት ፕሬዚዳንት ከክቡር ሃይምሂ ርቶግን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከክቡር ይስሐቅ ሻሚር ከከተማው ከንቲ ባና ከሌሎች የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ጋር ተወያይተው ስለዴ ር ሡልጣን ይዞታችንና ስለ ቅድስት ገዳማችን ስለ ኢትዮጵያና እሥ ራኤል ጥንታዊ ግንኙነት አንስ ተው ከአጥጋቢ ውጤት ደርሰዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስና በእሥራኤልና በሌሎች ሀገሮች ስለ አደረጉት ጉብኝት ለጋዜጠኞችና ለቴሌቪገርን ሪፖርተሮች መግለጫ ሰጥተዋል ።

ቅዱነነታቸው በሰጡት መግለጫ «በእስራኤል መንግሥትና ሕዝብ የተደረገላቸው ከፍተኛ አቀባበል ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል አክ ብሮት ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ባለሥልጣኖችን አመስግነው ከቅድ ስት ሀገር ኢየሩሳሌም ጋር ኢት ዮጵያና የኢትዮጵያ ምእመናንያላቸ ውን የረጅም ጊዜ መተሣሠርና የመልካም ግንኙነት ታሪክ ወደ ፊትም እንደሚቀጥል ገልጸዋል ።

በተለይ በዴር ሡልጣን ስለሚ ፈጠረው ችግር ክቡር ፕሬዚዳንት የመጨረሻ መፍትሔ እንዲሰጡት ቅዱስነታቸው ላቀረቡት ጥያቄ በእ ሥራኤል መንግሥት በኩል መፍ



ትሔ የሚያስገኝ ምላሽ እንዲሰጥ ገልጸው ቅዱስነታቸው ለክቡር ፕሬ ዝዳንቱ የመታሰቢያ ስጦታ አድ ርገውላቸዋል ፓትርያርኩ ከክብር ከታዮቻቸው ጋር ግንቦት ፲ ቀን ፹፩ ዓ/ም ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር የሚገኙትን ጥንታውያን የሆኑትን የቅ/ ሥላሴን ና የቆሮንቶስን ገዳማት በኢያሪኮ የኤልሣቤጥን ምንጭ የጨውባሕርን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር ቶስ የተጠመቀበትን ቦታ ተዘዋ ውረው ጎብኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በእስራኤል የሚያደርጉትን ጉብኝት አጠናቀው ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ከቴልአቢብ ተነሥተው በግ ሪግ የሚያደርጉትን ጉብኝት ለመ ጀመር አቴንስ ከተማ ሲገቡ በግ ሪክ የኢትዮጵያ አምባሳደር ጓድ ሳሙኤል ተረፈ የግሪክ ኦርቶዶ ክስ ቤተ ክርስቲያን ቅ/ሲኖዶስ ም/ፕሬዚዳንት በግሪክ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሠራተችኞ በአዲስ አበባ የግሪክቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የሀ ገሪቱ ጋዜጠኞችና የቴሌቭዥን ሪፖ ርተሮች በአሎምፒክ አየር ማረ ፊያ ደማቅ አቀባበል አድርገውላ ቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ስለተደረገላቸው አቀባበልና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ስለ አለው ሁኔታ ለጋዜጠኞች መግ ለጫ ሰጥተዋል ።

በማግሥቱ እሑድ የግሪክ መን ግሥት ለኢትዮጵያውያንምእመናን በሰጠው ቤተ ክርስቲያን ቅዱስነታ ቸው ሲደርሱ በርከት ያሉ ምእመ ናን እንኳን ደኅና መጡ በማለት ደማቅ አቀባበል ካደረጉላቸው በኋላ ቅዱስነታቸው ቤተ ክርስቲያኑን ባርከው የቅዳሴው ሥርዓተ ጸሎት መሪ በመሆን ከተከታዮቻቸው ጋር ቀድሰው ለምእመናንቍርባን ከአቈ ረቡ በኋላ በቅዳሴው መጨረሻለምእ መናኑ በሰ ጡት ትምህርትና ቃለ ቡራኬ ምእመናኑ ሀገራቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲወዱና እንዲ ያከብሩ ትምህርታዊ መመሪያ ሰጥተ ተዋል ።

ፓትርያርኩ በግሪክ ያሉትን ቅዱ ሳት መካናት ከክብር ተከታዮቻ ቸው ጋር ተዘዋውረው ጎብኝተ ዋል ። በግሪክ የሚማሩትን የኢት ዮጵያውያን ተማሪዎችም አነጋግ ረዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬ ዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳት ዘኢትዮጵያ በተለያዩ አገሮች ያደረጉት ጉብኝት ፈጽመው ግን ቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ከጧቱ ሁለት ሰዓት ላይ አዲስ አበባ ገብተዋል ።

## የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፩ኛ / ዓመት በዓለ ሢመት በከፍተኛ ድምቀት ተከበረ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆ ሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳት ዘኢትዮጵያ የመላዋ ኢትዮ ጵያና በዓለም ዙሪያ የምትገኘው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ፬ኛ ፓትርያርክ ሆነው የተ ሾሙበት ፩ኛ ዓመት ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም በመላዋ ኢት ዮጵያ በከፍተኛ ድምቀት ተከብር ውሎአል ።

በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅዱስነታቸው በተገኙ በት ከፍ ባለ መንፈሳዊ ሥነ ሥር ዓት ተከብሮአል ። ለበዓሉ አከባ በር በወጣው መርሐ ግብር መሠ ረት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥ ላሴ ካቴድራል ቅዳሜ ለእሁድ አጥ ያ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ጀ ምሮ ሊቃውንት ፣ መዘምራን ካህ ናት ለበዓሉ የሚገባውን ጸሎትና ማኅሌት ሲያደርሱ አድረዋል ። ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ፣ ሲሆን ከየአድባራቱ የተውጣጡ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስና ዲያቆናት ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን በካቴድራሉ ተገኝተው የተመደበላቸውን ቦታ እንደያዙ አሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪ ዎች ፡የሰበካ ጉባኤ ም/ሊቃነ መና ብርት ጥሪ የተደረገላቸው እንግ ዶች እጅግ በዛ ያሉ ምእመናን በሥፍራው ተገኝተው በመጋቢ ካህ ናቱ አስተናባሪነት የተዘጋጀላቸው ን ስፍራ ይዘዋል ።

ከሌሊቱ ለ፲፪ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መር ቆሬዎስ ፓትርያ ርክ ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በብፁዓን ሊቃ ነ ጳጳሳት ታጅበው መንበረ ጸባ ኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሲደርሱ ለአምስት ደቂቃ ያህል የቤተ ክርስቲያኑ ደወል አስተጋ ብቷል ።

ቅዱስነታቸው ከካቴድራሉ ሲ ደርሱ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪ ሁን የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ተወካይ ከጠ ቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላ ፊዎች ጋር በመሆን አቀባበል አድ ርገውላቸዋል ።

በዚሁ ወቅት ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት ፣ የወርቅና የብር የመጾረ መስቀል በመያዝ ዩኒፎርም የለበሱ የሰ ንበት ት/ቤት ተማሪዎች

«ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግ ዚአብሔር » የሚለውን ግሥ እየ ዘመሩ በደማቅ ሁኔታ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ከ፲፪ ሰዓት ጀምሮ በቅዱስነታ ቸው መሪነት ፣ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ድረስ ሥርዓተ ቅዳሴው ተከናው ኖአል ።

የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት እንደ ተፈጸመ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መ



www.ethiopianorthodox.org



ቅዱስ ፓትርያርኩ በበዓለ ሢመቱ ዕለት በዐውደ ምህረቱ ላይ በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ እንደተገኙ ።

ርቆሬዎስ በዐውደ ምህረቱ በተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ እንደ ደረሱ የተፈቀደላቸው ሦስት ሊቃውንት ከቅዱስነታቸው ፊት ቀርበው ፤

«አንተ ውእቱ መርቆሬዎስ ፓ
ትርያርክ
ዘላዕለ ኵሉ ሢመት ዘላዕለ ኵሉ
ወኵሉ ስም ዘይሰመይ በበዓ
መት ዘይሰመይ ታስተፌሥሕ
ልበነ ዘላዕለ ኵሉ ኄር»
«እቀድም አእኵቶቶ ለእግዚአ
ብሔር
ለዘአብጽሐነ ያብጽህክሙ በበ
ዓመት»

የሚለውን ግሥ ከቃኙ በኋላ መዘምራት እጅግ በደመቀ ሁኔታ አሸብሽበው እንዳበቁ በሰንበት ት/ቤት አስተባባሪነት ከሰንበት ት/ቤት ተውጣጥተው ዩኒፎርም የ ለበሱ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች፤

«አሠርጎካ ለኢትዮጵያ በስ
ብሐት ወበሃሌ ሉያ ፤
መርቆሬዎስ ለቤተ ክርስቲያን
ባርከነ አባ መፍቀሬ ሕጻናት
መርቆሬዎስ ፤
እስመ አንተ ሰባኬ ወንጌል
ሐዲስ ፤
ሰባኬ ወንጌል መርቆሬዎስ»

የሚለውን ግሥ ቃኝተው ለአሥራ አምስት ደቂቃ ያህል በጸናጽልና በከበሮ አሸብሽበውታል ። እንደፕሮግራሙ ቅደም ተከተል ፤ ም የተፈቀደላቸው አራት ሊቃውንት ማለትም ርእሰ ማእምራን እንባቆም ቃለ ወልድ ንቡረ ዕድ ክፍለ ዮሐንስ

መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ መሪጌታ ቀጸላ መንግሥቱ ከቅዱስነታቸው ፊት እየቀረቡ ፤ አራት አራት መወድስ ቅኔዎችን አበርክተዋል ። ከዚህ ቀጥሎ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዓሉን አስመልክተው የሚከተለውን ቃለ ምዕዳን አስተላልፈዋል ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

«ይትባረክ እግዚአብሔር አቡሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘባረከነ በኵሉ በረከተ መንፈስ ቅዱስ ዘበሰማያት በኢየሱስ ክርስቶስ፤ በሰማያት በመንፈሳዊ ክብር ሁሉ ያከበረን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አባት እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ። (ኤፌሶን ፩፡፫) ።

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፣ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ፣ በዚህ በዓል ላይ የተገኛችሁ እንግዶችና የተወደዳችሁ ምእመናን ይህ ቀን የአንድን የቤተ ክርስቲያን ኃላፊ በዓለ ሢመት ብቻ የምናስብበት ዕለት ሳይሆን ቤተ ክርስቲያናችን በእግዚአብሔር ፈቃድ በራስዋ አበው ራስዋን ለመምራት የቻለችበትን የበረከትና የጸጋ ዕለት በደስታ እያስታወስን በመንፈሳዊ በረከትና ሁሉ ለባረከ አምላክ ምስጋና የምናቀርብበት ዕለት ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንታውያን የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ ናት ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ምንረዳው የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ የተሰበከው በመጀመሪያው ምእት ዓመት (፴፬) በኢትዮጵያዊው መልእክተኛ በሕጽዋ ለሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ እንደ ሆነ ይታመናል («የሐ-ሥ - ፰፡፳፮ ።) ቅዱሳን ሐዋርያትም ማቴዎስና እንድርያስ በኢትዮጵያ ወንጌልን ማስተማራቸው በታሪክ ተረጋግጦአል ። ይሁን እንጂ ክርስትና በኢትዮጵያ የተስፋፋውና የተጠናከረው በ፬ኛው ምእት ዓመት ሲሆን ይኸውም መጻሕፍተ ሐዲሳትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ይዞ በመጣው በቅዱስ ፍሬምናጦስ ነበር ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ኢትዮጵያዊ ጠባይና ባህል ያለው ትምህርተ ሃይማኖትዋን ጠብቃ እስከ ዘመናችን አቆይታለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት በቅዱሳት መጻሕፍት በአባቶች ትምህርት በሦስቱ ጉባኤያት ማለትም በኒቅያ በቁስጥንጥንያና በኤፌሶን በተወሰነው ትምህርተ ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ነው ። መለኮታዊ ጸጋ የሚሰጥባቸውን ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንም ትቀበላለች ፤ በእነርሱም ሥርዓት አምልኮትዋን ትፈጽማለች ፤ የቅዱሳንን አማላጅነት ታምናለች በትምህርተ ሥጋዌም በኩል እንደ ሌሎች ጥንታውያን የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ማለት እንደ እስክንድርያ ፤ አርማንያ ፤ ሶርያና ሕንድ የቅዱስ ቄርሎስን ትምህርት በመቀበል አንድ አካል አንድ ባሕርይ ብላ ታምናለች ታሳምናለች ።

ይሁን እንጂ የራስዋን ትምህርትና እምነት ታሪክና መብት በመጠበቅ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር አብሮ ለመሥራትና ለመረዳዳት ስለ ዓለም ሰላም ፤ ስለ ሕዝቦች እኩልነትና መብት ነጻነትና ፍትሕ አስፈላጊነት ለመመስከር ዓለም አቀፋዊ አንድነትን ትደግፋለች ስለዚህም በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባላት አንድዋ ናት ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በበዓለ ሢመቱ ምክንያት ለተሰበሰበው ሕዝብ ቃለ ምዕዳን ሲሰጡ ።

በመሆኑም ማኅበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ስለ ተራድኦ ፤ ስለ ሰላም ስለ ስደተኞች ፤ ስለ ሌላውም ሁሉ በኅብረት መጸለይንና መሥራትን አላቋረጠችም ወደፊትም አታቋርጥም

ይህች ሐዋርያዊት ጥንታዊትና ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያናችን እስካሁን ተጠብቃና ተከብራ የቆየችውና ለአፍሪካ ሕዝብም መመኪያ ሆና የኖረችው በተከታዮችዋ አንድ ነት መሆን አይዘነጋም ።

አሁንም ይህች ቤተ ክርስቲያን ለተተኪው ትውልድ ታሪካዊ ትርስዋን፣ትምህርቷንና ሥነ ጥበብዋን ማስተላለፍ የምትችለው አገልጋዮችዋ ካህናትና ተከታዮችዋ ምእመናን ተባብረው ሲጠብቋትና ሲደግፏት ነው ። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ኢትዮጵያም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተነጥላ የምትታይ አይደለችም ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያንዋ ታሪክ የሀገሪቱ ታሪክ የሀገሪቱ ታሪክም የቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ነውና ስለሆነም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለዚህች ለቅርስ ፤ ለታሪክና ለባህል ፤ ለሥነ ጽሑፍና ለትምህርት ነባር ምንጭ ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሊያስብ ይገባዋል ። ካህናትና ምእመናንም እንደአንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ አሳቢ ሆነው ለቤተ ክርስቲያናቸው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት መሟላት የየበኩላቸውን ተልእኮ መፈጸም ይኖርባቸዋል ።

እንዲህ ከሆነ ለሀገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን የሚበጅ ሥራ መሥራት እንችላለን። ከቀደሙ አባቶች የወረስነውም ይህ የአንድነት ጠባይ ነው ፤ እግዚአብሔር አምላካችንም የአንድነትና የሰላም አምላክ እንጂ የመለያየት አምላክ አይደለም ። አንድነታችን ከጠነከረ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎታችን የተሟላ ይሆናል ። እንዲሁም ከእምነት ጋር አንድነት ካለ ስንኳንስ ለኢትዮጵያ ለአፍሪካ በሙሉ ወንጌልን ለመስበክ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን በምልዓት ለማበርከት እንችላለን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና አሁንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሱዳን ፤ በኬንያና በጅቡቲ ቤተ ክርስቲያን አቋቁማ መንፈሳዊና ማ





www.ethiopianorthodox.org

ኅበራዊ አገልግሎትዋን እያበረከ ተች ነው ።

ወደፊትም የቤተ ክርስቲያናች ንን አገልግሎት በመፈለግ ካህን እንድንልክላቸው ቤተ ክርስቲያን እንድናቋቁምላቸው የሚጠይቁ ብ ዙዎች ናቸው ።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አም ላክ ቤተ ክርስቲያኑን እንድንጠ ብቅ መንጋዎቹ ምእመናንን እንድ ንመግብ መንፈሳዊ ኃላፊነትና አደራ የጣለብንን ያህል ወንጌል ን ለሁሉ ለማዳረስ ስለሰው ል ጆች መብትና እኩልነት ለመሥ ራት የሰው ልጅ ጠላቶች የሆኑ ትም ረኃብ በሽታና ድንቁርና የሥነ ምግባር ውድቀትና በእነር ሱም ጠንቅ የሚመጣው ችግር ሁሉ እንዲወገድ የሚፈለገውን የመ ንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለመፈጸም መትጋት ከቤተክርስቲ ያን አገልጋዮች ሁሉ የሚጠበቅ ግዴታ ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችን ባለፈው ዓመት የፈረሱ አብያተ ክርስቲያ ናት እንዲታደሱና አዲስ የሚሠ ሩትም ፍጻሜ እንዲያገኙ ፤ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዲጠናከ ር ስብከት ወንጌል ለሁሉም እን ዲዳረስ የሰንበት ትምህርት ቤቶችም እንዲስፋፉ ፤ እንዲሁም ድርቅ ባስከተለው ችግር የተጎዱ ወገኖች እንዲረዱ ወዘተ ፣ ያደረ ገችው ጥረት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ወደፊትም ይህ ዓይ ነቱን ተልእኮ ለመፈጸም ትጥራ ለች ።

ይህን መንፈሳዊ የቤተ ክርስ ቲያናችንን በዓል ለማክበር ከዚህ የተገኛችሁትን ሁሉ እግዚአብሔ ር ይባርካችሁ በረድኤቱ ይጠብ ቃችሁ ሰላሙን ይስጣችሁ ።

አገራችን ኢትዮጵያን እግዚአ ብሔር በአንድነትና በነጻነት ይጠ ብቅልን ለሕዝባችን ሁሉ አንድ ነትን ደኅንነትና ሰላምን ይስጥ ልን ለዓለም ሁሉ ሰላሙንና በረከ ቱን ያድልልን አሜን ።

ቀደም ሲል ግን መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን የጠቅላይ ቤተ ክህ ነት ሥራ አስኪያጅ ተወካይ በአ ንድ ዓመት ውስጥ ቅዱስነታቸው ለቤተ ክርስቲያን እና ለሀገሪቱ ለማህበራዊ ጉዳዮች ያበረከቱትን ከፍተኛ ሥራ ዘርዝረው በመግ ለጽ ንግግር ያደረጉ ሲሆን ወደ ፊት ሊሠሩ ስለታቀዱት ሥራዎ ችም አብራርተው አስረድተዋል በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ገብር ኤል ሊቀ ጳጳስ የትንግሌ ማኅ ተሚያ ድርጅት የበላይ ኃላፊ ቅዱስ ሲኖዶሱን በመወከል ንግግር አድርገዋል ።

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ቡራኬ ሰጥተው በዚያ የሚከናወነው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።


ፓትርያርኩ ርዳታ ሰጡ ፤

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬ ዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃ ዳቸው ሆኖ ለደቡብ ኦሞና ለአ ርሲ አስተዳደር አካባቢ ፵ ሺህ ብር ጥሬ ገንዘብና አንድ ሺህ ካርቶን ግምቱ ፹ ሺህ ብር የሆነ የምግብ ዘይት ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ሰጥተዋል ። በቅ ዱስ ሲኖዶስ የመሰብሰቢያ አዳ ራሽ በተከናወነው በዚሁ ስጦታ ጊዜ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የበ ዓሉ ተካፋይ እንግዶች የልዩ ልዩ ሃይማኖት መሪዎች ተገኝተዋል ።

በዚህም መሠረት በደቡብ ኦሞ አስተዳደር አካባቢ ለሚገኙ ወገ ናቻችን ት/ቤት መርጃ እንዲሆን የብር ፲ ሺህ ቼክ ጓድ ተፈራ እን ዳለው የአካባቢው አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ ከቅዱስነታቸው የተረ ከቡ ሲሆን ሰማንያ ሺህ ብር ግምት ያለው የምግብ ዘይትም በደቡብ ኦሞ አስተዳደር አካባቢ ለሚገኙ ችግር ለደረሰባቸው ወገኖችን እር ዳታ እንደሚውል ተገልጿል ።

በስጦታው ሥነ ሥርዓት ላይ ቅዱስነታቸው ባደረጉት ካግገር ፤ «በአርሲ አስተዳደር አካባቢ ወገናቻቸውን አጥተው አሳዳጊ ላጡ ሕጻናት ማሳደጊያ በኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን አማካይነት የሕጻናት ማሳ ደጊያ እንዲቋቋምላቸው በመደረጉ ለዚሁ ት/ቤት መደጎሚያ እንዲ ውል ብር ፴ ሺህ መስጠታቸውን ገልጸው ወደፊትም እርዳታው እን ደሚቀጥል አረጋግጠዋል ።

እንዲሁም በ፲፱፻፹፮ ዓ/ም የበ ጀት ዓመት ከሌሎች የርዳታ ሰጭ አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት ጋር በመተባበር በደቡብ ኦሞ አስተዳደር አካባቢ ለሚገኙ ፲ ሺህ ያህሉ ችግረኞች ወገና ቻችን የመልሶ ማቋቋም መ ርሐ ግብር ቤተ ክርስቲያኒቱ በሥራ ላይ ለማዋል ማቀዷን አስረድተ ዋል ።



በበዓሉ ዕለት የተፈቀደላቸው ሦስት መዘምራን ግሡን ሲቆኙ ፣



ጓድ እንዳለ ተፈራ የአስተዳ ደር አካባቢዋና አስተዳዳሪ የእር ዳታውን ቼክ ከተቀበሉ በኋላ ባደ ረጉት ንግግር ።

የደቡብ ኦሞ አስተዳደር በኢ. ሕ. ድ. ሪ. አዲስ የአስተዳደር አወቃቀር መሆኑን ገልጸው ይህ አካባቢ በጣም ተረስቶ የቆ የና በአሁኑ ወቅት መንግሥት ትኩ ረት ሰጥቶት ማንኛውም ነገር እን ዲሟላ ጥረት እየተደረገ ነው ብለ ዋል ።

ኢያይዘው እንደገለጹትም ብፁ ዓን አባቶች አካባቢውን እየተዘ ዋወሩ እንዲጎበኙትና በዚያ አካ ባቢ የሚኖሩ ወገኖችን ከአ ውሬ ያነሰ ኑሮ ስለሚኖሩ እነዚህ ወገኖች የሕይወት ልምላሜ እን ዲያገኙ በሚደረገው ጥረት እኔና የሥራ ጓደኞቼ በዚሁ ጥረት ወቅት በመመደባችን የበለጠ ደስታ ይሰ ማናል ።

ቀድሞም ሆነ አሁን የምንኮራ ባት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚያ አካ ባቢ ቀደም ሲልም ከፍተኛ ርዳታ አድርጋ አምስት ሕንጻ አክል ድን ኳኖች በመለገሷ በአሁኑ ሰዓት ከ፭፻ በላይ ሕጻናትን አሰባ ስበን በማስተማር ላይ እንገኛ ለን ብለዋል ። በመጨረሻም ባሰ ሙት ንግግር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃ ነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በአካባቢው ለሚገኙ ወገኖቻችን ችግር ትኩ ረት ሰጥተው ስለአደረጉት ልገ ስናና ወደፊትም ስለታቀደው ርዳታ አመስግነው ለአካባቢው ነዋሪዎች የተሰጠውን ንብረትና ገንዘብ በት ክክል ለተጠቃሚዎቹ አገልግሎት ለማዋል ቃል ገብተዋል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለነ ዚህ ወገኖቻችን የመጀመሪያ ወለላ የሆነውን ስጦታ በመረከቤ ከልብ አመሰግናለሁ ብለዋል ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስነታቸው ቡራኬ ሰጥተው የበዐሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

ተስፋ ጥሩነህ



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ሩፋኤል ሊ/መላእክት

ቅዱሳን መላእክት በተራዳኢነታቸው የአዳም ልጆችን ችግርና መከራ ሲያስወግዱ የሚኖሩ የልዑል እግዚአብሔር ባለሟሎች ናቸው ቅዱስ ሚካኤል ፡ ቅዱስ ገብርኤልና ሌሎች ነገደ መላእክት ሁሉ በአማላጅነታቸው በምድር ላይ የተለያየ ምህረተ እግዚአብሔር የሚያወርዱ ሰዎችን ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ እየመለሱ በልዩ ልዩ ትሩፋት አሸብርቀው የእግዚአብሔር ወገኖች እንዲሆኑ የዘወትር ተግባራቸው አድርገው የሚኖሩ ናቸው ።

ከነዚህ መጋብያነ ምሕረት ሊቃነ መላእክት አንዱ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሩፋኤል ነው የቅዱስ ሩፋኤል ተአምር በምናነብበት ወቅት ብዙ ሰዎች ከደረሰባቸው ልዩ ልዩ መከራ በእግዚአብሔር ኃይል ድነው በመልአኩ አማላጅነት ባለሟሎች ሁነው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በርትዕት ሃይማኖት ጸንተው መኖራቸውን እንረዳለን ። ለምሳሌ ያህል አቶ ይስሐቅ አብርሃም ትኳቦ በዚሁ መልአከ ረድኤት ከከፉ በሽታና ከአሰቃቂ መከራ ሊድኑ ችለዋል ።

አቶ ይስሐቅ አብርሃም ሾፌር ናቸው የካቲት ፳፯/፲፱፻፸፪ ዓ/ም በመሥሪያ ቤታቸው ተልከው ወደ ወለጋ ይሄዳሉ ከግምቢ ወደ ደንቢዶሎ በጉዞ ላይ ሳሉ በቂጦ በረሀ አንድ ትልቅ ዝንብ መሳይ ከቀኝ ዓይናቸው ጠርዝ ላይ አከታትሎ ሦስት ጊዜ ይነድፋቸዋል፤ ለጊዜው ቢያሳክካቸውም ከጥቂት ቀናት በኋላ ማሳከኩን ተዋቸው ።

ነገር ግን ከሁለት ወር በኋላ ከዓይናቸው መሐል ላይ ነጭ ነገር ሸፈነው በዚሁ ጊዜ የነበሩት ደንቢዶሎ ነው ጓደኞቻቸው አባ ፊልጶስ የሚባሉ የዓይን ሐኪም በዚያው ነበሩና ሄደው እንዲመረመሩ ስለጠቆሙአቸው ሄደው ቢመረመሩ ጥሎብሃልና ለማንሣት አይቻልም ብቻ ከሁሉ የሚበልጠው በእግዚአብሔር መታመን ነውና ሁል ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ ብለው አሰናበቱአቸው ።

ከዚያም አዲስ አበባ እንደተመለሱ የመ/ቤቱ ክሊኒክ ሁኔታውን በማየት ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ላካቸው በሆስፒታሉ ለምርመራ ከገቡ በኋላ ጠብታ ተሰጥቶአቸው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

ይሁን እንጂ የተሰጣቸው ጠብታ ምንም ለውጥ ስላላስገኘላቸው መኪና እየነዱ በከፍተኛም ሆነ በአነሥተኛ ፍጥነት በሚጓዙበት ወቅት ደህነኛው ዓይናቸው ላይ አቧራ ገብቶባቸው ለመጥረግ ሲፈልጉ በአደጋ ላይ ስለሚጥላቸው ለከፍል አለቆቻቸው ቢያሳዩአቸው እንደገና እንዲመረመሩ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተላኩ ።

ለሁለተኛ ጊዜ ለምርመራ ቀረቡ እንደአጋጣሚ ዶ/ጳውሎስ ነበሩ ያጋጠሙአቸው እርሳቸውም እንደጣለባቸውነገሩአቸውና ከጀመረህ ስንት ቀን ሆናአል አሉአቸው ሦስት ወር መሆኑንም ነገሩአቸው እንዲህ ዓይነቱ በሽታ የሚይዘው በልጅነት ዘመን ነበር አንተ ግን እንዴት አሁን ሊይዝህ ቻለ ? አሉአቸውና ጠብታ አድርገውላቸው ለአራት ቀን ቀጠሮ ሰጡአቸው ።

አቶ ይስሐቅ አብርሃም በተሰጣቸው ቀነቀጠሮ ወደ ሆስፒታሉ ቢሄዱ ሐኪሞቹ (ዶክተሮቹ) የሉም ተብለው እንደገና ለሳምንቱ ተቀጠሩ አሁንም በሳምንቱ ወደ ሆስፒታሉ ሄዱ ነገር ግን ዛሬም ሐኪሞች በማስተማር ላይ ስለሆኑ ለሳምንት ቀጠሮ ስለሰጡዋቸው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

ሦስተኛው ቀጠሮ ተጠርተው ገቡ ሆኖም በመጀመሪያ የመረመሩአቸው ዶክተር ጳውሎስ ሳይሆኑ ሌላ ስለነበሩ ሁኔታውን ዓይተውሊገፈፍ አይቻልም ምናልባት ዶክተር ጳውሎስን አማክረን እሚሆን ከሆነ በአፕሬሽን ጥሌኑ ሰፋ ብሎ ነው በመሐል ብቻ እንድትቀር ለማየት እንዲረዳህ ይደረግ ይሆናል ብለው ለሳምንት ቀጠሮ ሰጡአቸው በቀጠሮው ቀን ተመልሰው በቀረቡ ጊዜ ዶክተር ጳውሎስ ነበሩ የተሰጣቸው ተስፋ ግን አልሆነም ።

መገፈፍ አይቻልም ምናልባት ከቻልክ ከአንድ ዓመት በኋላ እንድትመጣ አሉአቸው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በሰው ይፈጸማል (ይደረጋል) የሚለው ተስፋ ከአቶ ይስሐቅ አእምሮ ተፋቀ መዳን ከከባድ ሥቃይና መከራ መላቀቅ በእግዚአብሔር ኃይል ይቻላል እንጂ በሰው ዕውቀትና ጥበብ ይሆንልኛል ብዬ አልገምትም ስለዚህ ከዚህ ቀን ጀምሮ ወደፈጣሪዬ ብቻ እማጸናለሁ በማለት ጠዋትና ማታ ወደ እግዚአብሔር ልመናቸውን ማቅረብ ጀመሩ ።

ስለዚህ ከዕለታት አንድ ቀን ወሩ ነሐሴ ጾመ ፍልሰታ ነበር መቼም አቶ ይስሐቅ በሥራ ገበታቸውም ሆነ ከሥራ ሲወጡ ጸሎታቸውን ወደ እግዚአብሔር ከማቅረብ አላቋረጡም በተለይም በጉዞላይ ሳሉ ሻሸመኔ መንገድ ከነገሌ አርሲ ወዲህ ፪፻፹፭ ኪ/ሜትር ላይ ከመድኃኔ ዓለም ቤ/ክርስቲያን መኪናነቸውን አቁመው ይጸልያሉ ።

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ የተስፋ ፍንጭ አገኙ በዓይናቸው መሐል ተቋልሎ የነበረው ነጭ ጉም ዘረዘረላቸው ከጉዞአቸው ሲመለሱ ደብረ ዘይት ላይ ሲደርሱ ዘመዳቸው ወደ ሆኑ ወ/ሮ ገደይ ቤት ጎራ አሉ ምሳ ሲበሉ ወ/ሮ ገደይ ስለዓይናቸው ጠየቁአቸው እርሳቸውም ተስፋ ያገኙ መሆናቸውና የማየት ኃይል የጨመረ መሆኑንም ነገሩአቸው ።

በዚህ ጊዜ ወ/ሮ ገደይ እንዲያውም የቅዱስ ሩፋኤል ቅዳሴ ጸበል እምጥቻለሁና ብለው እምጥተው ሁለቱን ዓይናቸውን ቀቡአቸው ወዲያውኑ በርበሬ እንደገባበት የለበለባቸው መሆኑንና በፀበሉም መላ ሰውነታቸው የቀቡት መሆኑን አስረድተውናል በመጨረሻም አቶ ይስሐቅ ንግግራቸውን ሲያጠቃልሉ ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ጠዋት ተነሥቼ በመስታወት ዓይኔን ስመለከተው ነጭ ጉም ከዓይኔ ፈጽሞ ጠፍቶአል አላምንም ብዬ አልተደሰትኩም ምክንያቱም እውነቱ ነው ? ወይስ ዓይኔ በትክክል ስላላየልኝ ነው ? በማለት ነበር የተጠራጠርኩት በእርግጥ የጨለማ መጋረጃ ፈጽሞ መጥፋቱን ባረጋገጥሁ ጊዜ ግን ለካስ እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርግና በእርሱ የሚታመን ሁሉ ምንም የሚያጣው ነገር የለም ? በማለት በእምነቱ ላይ እምነት ጨምሬ እውነተኛና ፍጹም ክርስቲያን ለመሆን በቃሁ ሲሉ እግዚአብሔር በእደ መልአኩ ያደረገላቸውን ፈውስ በማድነቅ እምነታቸውን ከምስጋና ጋር ገልጸዋል ።

መርጌታ ፍሥሐ ባንተ

# ቅዱስ ዮሐንስ

ዮሐንስ ማለት ፍፁም ደስታና ፍቅር ሰላም ማለት ነው ይኸም ስም በአጋጣሚ የወጣ አይደለም እንድ ታላቅ ኃይል የተደረገበት አስደናቂ ተአምርም የታየበት ነው ።

ይኸውም ካህኑ ዘካርያስና ሚስቱ ኤልሳቤጥ እግዚአብሔርን የሚፈሩ በሃይማኖት የጸኑና ሁለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ጽኑ ግንኙነት ያላቸው ቅዱሳን ነበሩ ይሁን እንጂ ደግነታቸው በሕዝብ የታወቀና በእግዚአብሔር የጸደቀ ቢሆንም ዓይናቸውን የሚያሳርፉበት ልጅ አልነበራቸውም በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው ዘወትር ወደ እሱ እየመለከቱ ያዝኑና ይጸልዩ ነበር ።

ትንኘን ስንኳ የማይዘነጋ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ተቀብሎ ኀዘናቸውንም ተመልክቶ ልጅ እንዲሰጣቸው ቅዱስ ፈቃዱ ሆነ ። እንግዲህ በዘመነ ብሉይ የነበሩ ካህናት ቤተ መቅደስን ሲያገለግሉ በሳምንት በሳምንት እየተፈራረቁ በተራ ነበርና ዘካርያስ የሚያገለግልበት ሳምንት ደርሶት መሥዋዕትን ለመሠዋት ጸሎተ ዕጣንንም ለማድረስ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ሲያጥን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከዕጣኑ መሠዊያ በስተቀኝ ቁሞ ታየውና ከዚያ በፊት መልአክአይቶ ስለማያውቅ ፈራ ደነገጠም መልአኩ ቅዱስገብርኤልም ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ እግዚአብሔር ፊት ደርሶልሃልና አትፍራ አትደንግጥ እነሆ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ስሙም ዮሐንስ ትለዋለህ ሰላምና ደስታ ይሆንልሃልና ብሎ ወንድ ልጅ እንደሚወልድ የምሥራቹን ከነገረው በኋላ ዘካርያስ እንደቃልህ ይደረግልኝ ብሎ በመቀበል ፋንታ ተጠራጠረ ፣ ምክንያቱም እሱም ሆነ ሚስቱ ሸምግለው የሚወልዱበት ጊዜ አልፎባቸው ነበርና ።

ሁኖም ዘካርያስ ዝም ብሎ አልቀረም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ለመሆኑ ልጅ ትወልዳለህ ስትለኝ ምን ምልክት ትሰጠኛለህ? በምን አውቀዋለሁ? ሲል ጥያቄ አቀረበለት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆም ነኝ የምሥራችንም እንድነግርህ ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ተልኬ ነበር ነገር ግን ቃሌን አምነህ ስላል ተቀበልክ ይህ ጉዳይ እስኪፈጸም ድረስ ድዳ (በሃም)ትሆናለህ መናገርንም አትችልም ሲል ምልክት ሰጥቶታል ። ከዚህ ላይ እንደ ተነ



ቅዱስ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

ገረው ድዳ ሳይሆን በሀም ሁኖ ነበር ዲዳ ማለት መናገርን የሚችል ሁኖ የረገ ፊደል ለ ብሎ የሚያነብ ነው በሀም ማለት ግን ፈጽሞ መናገር የማይችለው ነው ።

ዘካርያስም ልጁን እስኪወልድ ድረስ በሃም ሁኖ ነበር ከዚህ በኋላ የተጸነሰው ተወልዶ ዘመድ ቤተ ሰብ ሁሉ አንድ ላይ ተሰብስበ ማን እንበለው? ምን ብለን ስም እና ውጣለት? ሲባባሉ በመመካከር ዘካርያስን በእጃቸው ቢያመለክቱት ተዘግቶና በሃም የነበረው አፉ ተከፍቶ ዮሐንስ ይባል ሲል ተናገረ ምክንያቱም ልጁ ከተጸነሰበት ጀምሮ እስኪወለድ ድረስ በሃም ሁኖ የነበረው ካህኑ ዘካርያስ ዮሐንስ ሲወለድ አፉ ስለ ተከፈተና ልጅ ሲወለድ ደስታ ይሆንልሃል ተብሎ የተነገረውም ትንቢት ተፈጸመለት ከዚህ ላይ ዘካርያስ እጅግ ድርብ ደስታን ነው ያገኘ ይኸውም ፩ኛ ልጅ ያልነበረው ልጅን ማግኘቱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተዘግቶ የነበረው አፉ ተከፍቶለታል ።

ከዚህም ላይ ለይቶ ማወቅ የሚገባ ነገር አለ በሐዲስ ኪዳን ዮሐንስ እየተባሉ የሚጠሩ ብዙዎች እንዳሉ ግልጽ ነው ምሳሌ መጥምቁ ዮሐንስ ወንጌልን የጻፈ ዮሐንስ ማርቆስ የተባለ ዮሐንስ በመባል ይታወቃሉ ግን መስከረም ፩ እና ፪ ቀን የሚውለው ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የትኛው መሆኑን ለመግለጽ ያህል ነው ።

ይኸውም አንዳንድ ሰዎች ወንጌላዊ ዮሐንስንና መጥምቁ ዮሐንስን አንድ ናቸው የሚሉ ስላሉ ነው ታዲያ መጥምቁ ዮሐንስና ወንጌላዊ ዮሐንስ አንድ ሳይሆኑ ሁለት ናቸው የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ እናቱም ኤልሳቤጥ የሚባሉ ሲሆኑ የወንጌላዊው ዮሐንስ ወላጆችም አባቱ ዘብዴዎስ እናቱ ማርያም ይባላሉ መስከረም ፩ ቀንና ፪ ቀን የሚከበረውም ወንጌላዊው ዮሐንስ ሳይሆን መጥምቁ ዮሐንስ ነው ።

ይኸውም ቀደም ሲል ነቢዩ ኢሳያስ ስለ እርሱ ትንቢት ተናግሮልታ ፤ የተናገረለትም ትንቢት የአዋጅ ነጋሪ ቃል የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ ለአምላካችንም ጎዳና በበረሐ አስተካክሉ ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል ጠማማውም ይቃናል ይላል ኢሳ ፵፥ ፫—፭ ይህ ትንቢት የተነገረው ለመጥምቁ ዮሐንስ ነበር ። አሁን ግን መጥምቁ ዮሐንስም ወንጌላዊተብሎይጠራል«ንሥሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማይ» መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና ንሥሐ ግቡ ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ያስተማረ እሱ ነውና መጥምቁ ዮሐንስ ንስሐ ግቡ ብሎ ያስተማር እንጂ ያን ጊዜ ሕገ ኦሪትአላለፈችም ሕገወንገልም አልተሠራችም ነበር መጥምቁ ዮሐንስ የነበረው በሕገ ኦሪትና በሕገ ወንጌል መካከል ነው ።

ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ የገለጽነው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መሆኑን ነው እንዲያውም ወንጌላዊው ዮሐንስ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር እንደ ነበር ወንጌሉ ይናገራል ይኸውም መጥምቁ ዮሐንስ የእግዚአብሔር በግ እነሆ ብሎ ሲናገር ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሰምተው ኢየሱስን ተከትለው ኼዱያላቸው አንዱ እንድርያስ ሲሆን ሁለተኛው ግን ወንገላዊው ዮሐንስ መሆኑ ታውቆአል ።

መጥምቁ ዮሐንስ ፊትን አይቶ የማያደላ በትምህርቱም የማይፈራ ትክክለኛውን ትምህርት ለሕዝብ ሲያስተላልፍ የነበረ መሆኑና በዚህም እውነተኛውን ትምህርት በማስተማሩ ብዙ ጸዋትወ መከራ ተቀብሏል ።

መጥምቁ ዮሐንስ ካስያዘውና ለሞት ካበቃው አንዱ በዘመኑ የነበረው የገሊላ ገዥ ሄሮድስ የወንድሙ የፊልጶስን ሚስት ስላገባና ዮሐንስም ተገቢ አለመሆኑን ለማስገንዘብ የወንድምህን የፊልጶስን ሚስት አታግባ ሲል በሕዝቡ መካከል ወቀሰው እንዳያገባም አወገዘው በዚህ እያዘነ ሲኖር የልደቱን ዕለት የሚያከብርበት ጊዜ ደረሰና መኳንንቱንና መሳፍንቱን የሴት ወይዛዝርቱንሁሉ ግብር አግብቶ ሲያበላ ሲያጠጣ የሄሮድያዳ ልጅ ዘፋኝ ነበረችና ከድግሱ መሐል ገብታ ሰው ሁሉ እየጠጣ ዘፈነችለት ፤ የዘፈነችውም ዘፈን ስለ ማረከው የምትፈልጊው ነገር ንገሪኝ እስከ መንግሥቴ እኩሌታ ድረስም ቢሆን እሰጥሻለሁ ሲል ቃል ገባላት እሷ ግን እንግዲያስ ከእናቴ ጋር ልማከር ብላ ወደ እናትዋ ሄደች ንጉሡ ሄሮድስ የመንግሥቴ እኩሌታም ቢሆን እሰጥሻለሁ ብሎኛልና ላማክርሽ መጥቻለሁ ምንን ስጠኝ ልበለው አለቻት እናትዋም ሄሮድስ ሁለተኛ ሚስት አድርጎ ይዟት ስለነበረና ዮሐንስም እሷንና ሄሮድስን ይወቅሳቸውና በሕዝብ መጮኽ ያጋልጣቸው ስለነበር ልጅዋን እንዲህአለቻት ሌላ ነገር እንዳትይ የዮሐንስን ራስ ቆርጠህ ስጠኝ በይው ከዚህ በኋላ እኩሌታ መንግሥት አልፈልገውም መንግሥቱ የእኛ ይሆናል ብላ መክራ ስደደቻትና ሌላ ነገር አልፈልግም የዮሐንስን ራስ ቆርጠህ ስጠኝ አለች እሱም ሴት የላከችው ሞት አይፈራም እንደሚባለው ዮሐንስ ያን ጊዜ አሳስሮት ወህኒ ቤት ስለነበር የዮሐንስን ራስ ቆርጠው እንዲሰጥዋት ብሎ አዘዘና ቆርጠው ሰጥዋት ዘፋኝዋም የመጥምቁ ዮሐንስ ራስ ይዛ መጥታ ለእናትዋ ግዳጅ ጣለችላት ፤

መጥምቁ ዮሐንስ ራሱን ለመቁረረጥ የደረሰው ስለ ሥጋ ሀብት ስለ ኃላፊው ሹመት ሳይሆን መንፈሳዊ ትምህርትን በማስተማሩና ስለ ሃይማኖቱ ባጭር ታጥቆ ስለተነሣ ነበር ሃይማኖት እስከ ዛሬ ድረስ ጸንቶ የኖረውና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየው ያለፉት አባቶቻችን ጀርባቸውን ለመቅሠፍት አንገታቸውን ለስለት እየሰጡ ነበር ። አሁንስ ሃይማኖታችንን እንዴት ባለ ሁኔታ ነው መጠበቅ የምንችለው?መስሎ በማደር ነው? ወይስ እንደ እነ ቅዱስ ዮሐንስ ትክክለኛውን ትምህርት በማስተማር እንደሚታወቀው ትክክለኛውን ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን እጽፍ ድርብ ዋጋ እንደሚያገኙ የሚታመን ሲሆን ትክክለኛውን ትምህርት በማያስተምሩ መምህራን በእንፃሩ እጥፍ ድርብ ፍዳ እንደሚጠብቃቸው አያጠራጥርምና ።

ሁላችን ዓቅማችን በሚፈቅድልን መጠን እነ ቅዱስ ዮሐንስን በምግባር በሃማይኖት እንድንመስላቸው የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ አይለየን ።

ከነፊ ርግብ ማርቆስ



# አቡነ አረጋዊ

በቀዳማዊ ምኒልክ የኦሪት ካህናት ከታቦተ ጽዮን ጋር ወደ ኢትዮጵያ አክሱም መጥተው ሕገ ኦሪትን አስተምረው እንደ ነበረ በታሪክ የተረጋገጠ ነው ። ኋላም ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካይነትና በቅዱስ ፍሬምናጦስ የክርስትና እምነት ወደ ሀገራችን ገብቶ ከኦሪት እምነት ጋር እንዲሰበክ ካደረገ ወዲህ ፤ በኢትዮጵያ ያለውን የወንጌል ትምህርት መስፋፋት ፤ የቤተ ክርስቲያን እድገትና የሕዝቡን እምነት ብርታት ሲሰሙ መንፈሳዊ ቅናት እያደረባቸው በየጊዜው ወደዚች አገር የገቡ ቅዱሳን ብዙዎች ናቸው ። ከነዚህም አንዱ አቡነ አረጋዊ ሲሆኑ ታሪካቸው ባጭሩ እንደሚቀጥለው ነው ።

ጻድቁ አቡነ አረጋዊ የትውልዳቸው አገር ሮሜ ሲሆን አባታቸው ይስሐቅ ፤ እናታቸው እድና ይባላሉ ። ዘራቸው ከሮም ነገሥታት ቢሆንም በዘር የማይኮሩ ፤ በሀብት የማይታለሉ ደገኞች ነበሩ አቡነ አረጋዊ እንደ ቤተ ክርስቲያን ደንብ በተወለዱ በ፵ ቀናቸው ሲጠመቁ በወጣላቸው የክርስትና ስም «ዘሚካኤል» እየተባሉ ሲጠሩ አድገዋል።

ኋላም አስተሳሰባቸውና የልጅ አዋቂ መሆናቸውን ያዩ የመንፈስ ቅዱስ ወንድሞቻቸው «አረጋዊ» ብለዋቸዋል ። አቡነ አረጋዊ ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ምኞታቸው ሁሉ በብሕትውናና በምንኩስና ተወስነው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነበር እንጂ የነገሥታት ዘር እንደ መሆናቸው በሀብትና በድሎት ለመኖር አያስቡም ነበር ። ወላጆቻቸው ግን ድረው ኩለው ለወግ ለማዕረግ አብቅተው ዘር እንዲያተርፉላቸው ነበር እንጂ እሳባቸው እንደዚህ አልነበረም ።

ጻድቁም የዚህን ዓለም ሹመትና ሽልማት ከምንም ባለመቁጠር የእናት አባታቸውን ቤት ትተው ገና በልጅነታቸው ወደ ዕርዕ በመሄድ እስቄጥስ በተባለው ገዳም ገቡ ። ከዚያም የገዳሙ አበምኔት አባ ጳኩሚስን እንዲያመነኩሱዋቸው ጠየቁ ። አባ ጳኩሚስም ምንኩስና ለማንም የማይቻል ከባድ ነገር መሆኑን አስረዱዋቸው ። አቡነ አረጋዊም የገዳሙን ሥርዓት በመጠበቅ ፤ የምንኩስናንም ትምህርት በመጠንቀቅ ለምንኩስና የሚያበቃቸውን ፈተና ስላለፉ በ፲፩ ዓመታቸው በዚህ ገዳም አባ ጳኩሚስ አመንኩሰዋቸዋል ።

ከዚህም በኋላ አቡነ አረጋዊ በኢትዮጵያ ያለውን የክርስትና እምነት ታሪክ በመስማት እሳቸውን ከመሳሰሉ ስምንት ቅዱሳን መነኮሳት ጋር ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በአክሱም አርፈዋል ። እነሱም ከአባታቸው ጋር ተስእቱ ቅዱሳን (ዘጠኙ ቅዱሳን) የሚባሉት ናቸው

ይህም የሆነው አልአሜድ በተባለው የአክሱም ዘመነ መንግሥት ሲሆን ንጉሡ ተቀብለዋቸው ትንሽ ቀን ከቆዩ በኋላ የእነሱ አንድ ላይ መቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ስላልታያቸው በተለያዩ ቦታዎች በመከፋፈል ማስተማር ጀመሩ ። የአቡነ አረጋዊ ድርሻ በትግራይ ክፍለ ሀገር በአድዋ አውራጃ በሚገው በደብረ ዳሞ ተራራ አካባቢ ስለ ነበረ የዚህን ተራራ ርዝማኔና አስገራሚነት በመመልከት ወደ እናቱ ላይ ወጥተው ለመገብኘት ፈለጉ ። ነገር ግን ዙሪያው ገደል ስለነበረ መውጫ አጡና ወደበአታቸው ተመለሱ ።

በዚህም እያዘኑ ሱባዔ ገብተው ሳሉ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል መ[illegible]ቶ አይዞህ ወደ ደብረ ዳሞ የምትወጣበት ዘንዶ ከእግዚአብሔር ታዝ[illegible]ልሃልና ተነሥ ውጣ አላቸው ። እሳቸውም ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ቢሄዱ የታዘዘላቸውን ዘንዶ በገደሉ አፋፍ ላይ አዩት ። የዘንዶውም ጅራት ወደ እሳቸውስለቀረበላቸው በእጃቸው ጨብጠው በመያዝ ወደዚህ ተራራ ለመውጣት ቻሉ ። በዚህም ቦታ ላይ ከዱር አራዊትና ከሰማይ አእዋፍ በስተቀር ምንም ሰው አልነበረበትም ። ለዚህም በመብቃታቸው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ የሌሊቱን ቁር የቀኑን ሐሩር ችለው ፤ በጾም በጸሎት ተወስነው ከቆዩ በኋላ ከአፄ ገብረ መስቀል ጋር ሆነው በዚህ ቦታ ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል፡

ቅዱስ ያሬድም የተነሣው በዚህ ዘመን ስለነበር ወደዚህ ተራራ በመውጣት ከአቡነ አረጋዊ ጋር ተገናኝቶ ቤተ ክርስቲያኑንም በማየት ደስ ብሎት ብዙ መዝሙሮችን ደርሷል ። ይህም ገዳም የብዙ መነኰሳትና መናንያን መኖሪያ በመሆን እስካሁን በኢትዮጵያ ከሚገኙት ታላላቅ ገዳማት አንደኛው ሆኖ ታሪኩን ይዞ ይገኛል ።

አቡነ አረጋዊ በደብረ ዳሞ የብዙ መነኰሳትና መናንያን መሪና አስተማሪ በመሆን ለብዙ ዘመናት ከቆዩ በኋላ እግዚአብሔር ተገልጾላቸው «ጸሎትህና ድካምህን ተቀብያለሁ ከዚህም ዓለም ድካም አሳርፍሃለሁ በስምህ የተራበ ያበላውን ፤ የተጠማ ያጠጣውን ፤ የታረዘ ያለበሰውን ፤ መታሰቢያ ያደረገውን ሁሉ እስከ ፲፭ ትውልድ እምርልሃለሁ» በማለት ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም በኋላ ቆመው ከሚጸልዩበት ቦታ መስቀላቸውንና መቋሚያቸውን ብቻ ሲገኝ እሳቸው ወዴት እንደሄዱ ባለመታወቁ ማትያስ የሚባለው ደቀ መዝሙራቸው ፈልጎ ሊያገኛቸው አልቻለም እሱን በፊት ከእንግዲህ ወዲህ በዓይነ ሥጋ አንገናኝም ብለውት ነበርና እያዘነ ተመልሶ ታሪካቸውን ጽፎአል እንደነዕዝራና እንደነሄኖክ ሥጋቸውን የሞት ጽዕር ፣ የመቃብር አፈር ሳያገኘው በሕይወተ ሥጋ እንዳሉ ተሠውረዋል ።

ይህም የሆነው በ፺፱ ዕድሜአቸው ጥቅምት ፲፬ ቀን በመሆኑ በዚህ ዕለት ቤተ ክርስቲያናቸው በታነፀበት ፣ ጽላታቸው በአለበት ቦታ ሁሉ በታላቅ ድምቀት ሲከበር ይኖራል ። ስለአቡነ አረጋዊ ታሪክ በአጭሩ ይህን አስታወስን እንጂ ከሕፃንነታቸው ጀምረው በዚህ ዕድሜያቸው የፈጸሙዋቸውን ታምራትና ትሩፋት በሰፊው ለመረዳት ከተፈለገ ገድላቸውን ማንበብ ይቻላል ።

አቡነ አረጋዊ ሕምሳለ ገነት ወደ ሆነችዋ ደብረ ዳሞ ለመውጣት ዙሪያው ገደል ቢሆንባቸውም በታዘዛቸው ዘንዶ ተንጠልጥለው በመውጣት ምኞታቸው እንደተፈጸመላቸውና ሀሳባቸው እንደ ተሟላላቸው በታሪኩ ተረድተናል ። ማናቸውም ምእመን እግዚአብሔርን ከልብ አምኖ የፈለገውን ነገር ሁሉ በጸሎት ከጠየቀ ምድራዊ ፍላጎቱ ቀርቶ ሰማያዊ ገነት መንግሥተ ሰማያትን እንደሚያገኝ አያጠራጥርም «ፈልጉ ታገኙላችሁ ለምኑ ይሰጣችኋል ፣ በር ምቱ ይከፈትላችኋል» በማለት ራሱ አረጋግጦታል ።

ጻድቁ ዘንዶው ይውጠኛል ወይም ይጥለኛል በማለት አልፈሩም ፣ አልተጠራጠሩም ። ምክንያቱም ፈጣሪያቸው ከእርሳቸው እንደማይለይ ጸሎታቸውም ወደሱ ደርሶ መልስ እንደሚያስገኝላቸው ያምኑ ስለነበር ነው ። «እስመ ዓዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር ኀበ ጻድቃን ወዕዝኑሂ ኀበ ሥዕለቶሙ» የእግዚአብሔር ዓይኖቹ ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደጩኸታቸው ነውና» የሚለው የቅዱስ ዳዊት ቃል በእሳቸው ተፈጽሟል ።

ይህም ለአንድ ዓላማ የተነሣ ሰው አሳቡን ከግቡ ለማድረስ በተነሣ ጊዜ በሚገጥሙት አንዳንድ አስቸጋሪ ነገሮች ፍርሃትና ጥርጣሬን ከልቡ አውጥቶ ከበረታ ነገሩ ፍጻሜ እንደሚያገኝለት ነው ። ነገር ግን ከተጠራጠረና ካወላወለ ድካሙ ሁሉ ከንቱ ሆኖ እንደሚቀር ነው ።

አቡነ አረጋዊ ደብረ ዳሞ ከወጡ በኋላ ድካማቸው ውጤት አግኝቶ ብዙ ትሩፋትን አድርገዋል ። ይህን የመሰለ ታላቅ ገዳም ሠርተው ለትውልድ አበርክተው አልፈዋል ። ስለዚህ ብዙ ድካምና ሥራ ለታላቅ ክብር እንደሚያበቃና ለትውልድም የሚተርፍ መልካም ታሪክና መታሰቢያ ሊያተርፍ እንደሚችል ከዚህ መማር ይቻላል ።

«ጻድቁን በጻድቁ ስም የተቀበለ ፣ የጻድቁን ዋጋ ይቀበላል» ተብሎ በወንጌል እንደተነገረ ፡ የአባታችን አቡነ አረጋዊን በዓል ስናከብር በስማቸው መታሰቢያን በማድረግ ከእርሳቸው በረከትን ከእግዚአብሔር ምህረትን ለማግኘት ነው ።

መ/መንክር ዋሴ

# የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅም

በድንቁርና መወገድ የተገኘው ጥቅም ከታወቀበት ዘመን አንሥቶ እስከ ካሬ ድረስ እንኳንስ ያላወቁ ደቂቁና አዋቂዎችም የእውቀት አድማሳቸውን ለማስፋፋትና ለጥበብ አብሮ አደጉ ለመሆን ይችሉ ዘንድ ያለማቋረጥ መጻሕፍት ማንበብ ይኖርባቸዋል ።

በይበልጥ ሴቶች ለመንፈሳዊም ሆነ ለሥጋዊ ሕይወታቸው መመሪያ አድርገው ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ መጻሕፍት አሉ እነሱም ቅዱሳት መጻሕፍትና ዘመናዊ መጻሕፍት ናቸው ። በተለይም ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ መንፈሳዊ ትምህርትን እየተመገቡ ፈሪሃ እግዚአብሔር በልቦናቸው አድሮ ለወገኖቻቸውና ለሀገራቸው ርዳታ ለማካፈል መልካም ሥራ ለመሥራት የሚችሉባቸውን የምግባር ብርሃናት ያሳያሉ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በተፈጥሮ ባገኙት ርኅራኄ መሠረት በልዩ ልዩ መንገድ ወገኖቻቸውን ለመደገፍ ይችላሉ ለነዳያን በመመጽወት የተራበን በማብላት ፣ የተጠማን በማጠጣት የተቸገረን በመርዳት ፣ የታመመን በመጠየቅ እና በማስታመም የሚያበረክቱት በጎ ምግባር የብዙን ሰው ሕይወት ለመጠበቅ ይረዳል የሌሎችን ችግር ማቃለል ደግሞ የመጀመሪያው የፍቅር ሕግ በመሆኑ «ሌሎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን እናንተም ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው» የሚለውን የታላቁን መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያስታውሳል ።

ሴቶች ከፍተኛመሥዋዕትነት ያለውን መልካም ምግባር ለመፈጸም የሚችሉትን በመንፈሳዊ አስተዳደጋቸውና የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በመከታተላቸው ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም ምክንያቱም መንፈሳዊነት ከሌላቸው የጭካኔ ባሕርይ ስለሚወርሱ ፍጥረት ሁሉ ከነርሱ የሚጠብቀው እርዳታ ይጐድልበታል የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል ስለሆኑ በጎም ቢሆን ክፉ በግድ ርዳታቸው ለችግረኞች መዳረስ አለበትና ነው ።

በዚህ ሁኔታ ሴቶች ርኅራኄን ገንዘብ ካደረጉ እንኳንስ ቤተ ሰቦቻቸውን አልፈው ተርፈው ሌሎችንም መርዳት ይችላሉ ለምሳሌ ክርስትና ባልተስፋፋበት ዘመን የተማረ የሰው ኃይል በማይገኝበት የእውቀት አድማሶች እንዲህ እንዲሆኑ በስፋት ባልተዘረጉበት ወቅት ሴቶች ወገኖቻቸውን በርኅራኄ ለመርዳት ያደረጉት ተሳትፎ በቀላል የሚገመት አልነበረምእነ ክርስቶስሰምራ እነ መስቀል ክብራ የመሳሰሉት በሰጡት ፍሬያማ አገልግሎት ታሪክ



ሲያስታውሳቸው ይኖራል ።

እንዲሁም በውጭ አገር በኩል ናይቲንግል በምሥራቃዊ ፍሎሬንስ (ኢታሊ) የነበረችው ወጣት በሽተኞችን በማስታመም በጦር ሜዳ ጉዳት ያገኛቸውን ጀግኖች በመርዳት በምታደርገው ርኅራኄ «የጨለማ ውስጥ መልአከ ብርሃን» ብለው ይጠሯት ነበር ኤልዛቤት ፍሎም በእስረኞች መካከል እየተዘዋወረች ለራበው እህል ለተጠማ ውኃ ለሕመምተኛ የሚያስረልገውን እርዳታ እየሰጠች በማገልገሏ የተመሰገነች ነበረች ።

የሕንድ ተወላጅ የነበረችው ረምቢ ሰባት ቋንቋ ከማወቋም በላይ በርኅራኄዋ የተመሰገነች ነበረችወላጆቻቸው ሞተውባቸው አንዳች ተስፋ የሌላቸው ሕፃናት የሚያድጉበት ኦርፋኔጅ (የሕፃናት ማሳደጊያ) አቋቁማ የመጀመሪያ ጊዜ ሁለት ሺህ ሕፃናት ሰብስባ በማሳደግ ለወገኗ ያካፈለችው ጥቅም እጅግ ከፍ ያለ ነበር ።

እነዚህ ሴቶች ተገቢ የሆነውን አገልግሎት ለመፈጸም የቻሉት ርህራኄን ገንዘብ በማድረግና መጻሕፍት የሚያዙትን ሕገ እግዚአብሔር በማወቃቸው ነው ይሁን እንጂ በራሳችን ኃይል እንደማንፈጽማቸው አውቀን መጻሕፍትን በማንበብ ያለፉትን የቅዱሳት እንስት ታሪክ በመገንዘብ በመንፈስ ቅዱስ እየተረዳን መፈፀም እንችላለን ብዙውን ጊዜ ይህንን የሚያደርጉ ሴቶች በአስተሳሰባቸውና በአኳኋዳቸው የመልካም ምግባር ምሳሌዎች መሆናቸው አያጠራጥርም ።

ስለሴቶች መልካም ምግባርና እምነት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አስተያየቶች ከሊቃውንት ዘንድ እንደተነገሩ (እንደተሰነዘሩ) ግልጽ ነው ከሊቃውንቱም መልካም የሴቶችን መንፈሳዊ ሕይወት አድንቆ ስለተግባራቸው የበኩሉን አስተያየት ያስፈረው « ቦልቴር መልካም ምግባሮችን የሚያስተምሩን ሴቶች ናቸው» ብሏል ።

ሴቶች መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነቡ በነዳጅ ኃይል እንደሚንቀሳቀስ መኪና ይሆናሉ ማለት አይደለም ቅዱስ መጽሐፍን በጥንቃቄ በማንበብ ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በማዛመድ አገባብና አጠቃቀማቸው እንዴት እንደሆነ ሊቃውንትን በመጠየቅ ትርጉማቸውን በሥራ ላይ በማዋል ነው በዚህ አኳኋን መንፈሳዊ የሆኑ በጎ ምግባሮችን እንዲሠሩ ይገፋፉቸዋል ። በዚህም ሕይወታቸው ሲመሩና አቅጣጫቸውን ሲለውጡ በሚያከናውኑት ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛሉ ሕይወታቸውም የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት ያድርበታል ይህ ከሆነ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በእንክብካቤ የሚጠብቁ ሴቶች ዘወትር ቅዱሳት መጻሕፍትን ከዓይናቸው ማራቅ አይኖርባቸውም ።

በይበልጥም ባለፉት ዘመናት በየዓመቱ ትርጉማቸው የተሳሳቱ መጻሕፍትን ፣ መጽሔቶችንና ትራክቶችን ከሚያሰሩ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ለመቆጠብ አጋዥ ኃይል ይሆናቸዋል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም እየተመላለሰ ያስተምር በነበረበት ወቅት ሰዱቃውያን የመጨረሻውን ትንሣኤ በማስመልከት «ሰባት ወንድማማቾች አንዲትን ሴት አገቧት በትንሣኤ ቀንስ ሰባቱ አግብተዋታልና ለማን ሚሽት ትሆናለች ሲሉ የተሳሳተ ጥያቄ አቀረቡለት እርሱም መጻሕፍትን አታውቁምና ትስታላችሁ እንጂ በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ስለሚሆኑ አያገቡም አይጋቡም» አላቸው ማቴ፡ ፳፪ ፣ ፳፫ ፣ ፴

ጌታችን እንዳለውም መጻሕፍትን አለማንበብና አለመረዳት ከእንዲህ ያለው ታላቅ ስህተት ላይ ይጥላል ። ይህም ሁኔታ በዚህ ዓለም ያሉ ሴቶች አንድ ወንድ ላንድ ሴት አንዲትሴትላንድወንድ የተባለውን ውሳኔ ጥሰው ሲፈቱ ሲያገቡ ይታያሉ ። ይህ ሊሆን አይገባም ። ይህም ሕግ በመጣሱ በየትኛውም ዓለም ፍቺ በዝቶ ይታያል ወደ ፍርድ ቤትም ወጣ ብለን ብንመለከት የፍርድ ቤቱን ግቢ ተፋችዎች አጣበውት ይታያሉ ። ይህም ለቤት መፍረስ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ልጆችም አሳዳጊ አጥተው እንዲንከራተቱና ጠባየ ብልሹም ሆነው ላገር ሸክም እንዲሆኑ ይዳርጋል ።

ይህም በመሆኑ አብዛኛዎቹ ሴቶች የመንፈሳዊ ሕይወታቸውን ብላሽነት ከመዘንጋታቸው የተነሣ ሁል ጊዜ ቅዱስ ቃሉን ባለማድመጥ መጻሕፍት ባለማንበብም ክርስቶስን በልብ እምነዋለሁ በሕይወቴ ምንም ለውጥ አላገኘሁም ቤተ ሰቤም ሰላም የለውም በማለት ራሳቸውን ያታልላሉ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ክርስቶስን ቢያምኑም እንኳ መጻሕፍትን አንብበው አልተረዱም ። ይኸውም የእግዚአብሔርን ኃይልና የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥቅም አላወቁምና ነው ።

ስለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቲቶ በጻፈው መልእክቱ «ሴቶች በአካሔዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የሚገቡ የማያሙ ፣ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ ቆነጃጅትም የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ ባሎቻቸውን የሚወዱ ልጆቻቸወን የሚያፈቅሩ ራሳቸውን የሚገዙ ንጹሖች በቤት የሚሠሩ በጎዎች እንዲሆኑ ምከራቸው» ብሎታል ቲቶ ፣ ፪ ፣ ፫—፭ ።

እንዳለውም ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ መልካምና የተወደደ ስለሆነ ሴቶች ጭምቶች በነገር ሁሉ የታመኑ መጻሕፍትን የሚያነቡና የሚረዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል

መጽሐፍ የማይወድ የማያነብ ሰው ከዓለም ጋር ግንኙነት የሌለውን ከበላዩ ሕይወት ፈጥሮ እየኀረፈ ሲያልፍ በጨለማ ዋሻ የተሸሸገውን ከጥበብና ከዕውቀት መንኖ የሸሸውን መናኝ ሰው ስለሚመስል ሴቶች እልጫ የሆነው ኑሮአቸው እንዲጣፍጥ ማኅበራዊ አኗኗር እንዲኖራቸው ፣ ሕይወታቸው ብርሃን እንዲሆን መጻሕፍትን ከማንበብ ወደኋላ አይበሉ ከማንበብ ይገኛል ጥበብ ተብሏልና ።

ወ/ት መዓዛ እስማማው



www.ethiopianorthodox.org

# በቃሉ የሚያምን ሁሉ ይድናል

ማንም ሰው በልዩ ልዩ ደዌ ሲያዝ ከበሽታው ለመዳን መድኃኒት አለ ወደ ተባለው ቦታ ሁሉ መኼዱ አይቀርም ከሥጋዊና መንፈሳዊ ደዌ ለመዳን ሳይሆን ከዚህ ዓለም ድህነትና ከሥጋዊ በሽታ ለመላቀቅ ጨለማን ተገን እያደረጉ ወደ አባይ ጠንቋይ የሚገሰግሡ ብዙ ናቸው ይሁን እንጂ እንደነ ዚህ ዓይነቱ ከንቱ ሰዎች በሥጋም በነፍስም መድኃኒት እንደማያገኙ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ ።

ስለዚህ በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙ በቃሉ መሠረት በሥጋም በነፍስም ለመዳን የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ በእመቤታችን ፣ በጻድቃንና በመላእክት ፣ በነቢያት በሐዋርያት ፣ ስም ወደ ፈለቀው ጸበል እየኼዱ ቃለ እግዚአብሔርን እየሰሙና እያመኑ ቢጠመቁ በቅጽበት ይፈወሳሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል የሚያምን ሁሉ እንደሚድን የታመነ ነውና ዛሬ በጻድቁ አባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ስም በፈለቀው ፀበላቸውና ለመታሰቢያቸው በስማቸው በታነፀው ቤ/ክርስቲያን የአባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስና የሐዋርያቱ የጴጥሮስ ወጳውሎስ ብርሃናተ ዓለም ዓመታዊ በዓል ዕረፍት ለማክበር በዚህ ቦታ የተገኛችሁ ሁሉ የእነዚህ አባቶች በረከትና ረድኤት ይደርባችሁ ።

ይህ ቦታ ጻድቁ አባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ የጸለዩበት ፣ የሰገዱበት ያረፉበት ስለሆነ እግዚአብሔር በጻድቁ አማላጅነት አምነው ፀበላቸው የሚጠመቁ ሁሉ ቸርነት ፈውስና ምሕረት እንደሚያገኙ በቃል ኪዳኑ አረጋግጦላቸዋል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በጾም በጸሎታቸው በሐዋርያዊ ተግባራቸውም መጠን ለዓለም ሁሉ የሚያበራ የክብር ብርሃን ስለሰጣቸው ቅዱስ ጻድቅ ብለን እንጠራቸዋለን ።

በ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከግብፅ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ የመጡት ርእሰ ባሕታውያን የሆኑት አባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዚሁ በተቀደሰ አርአያነታቸው መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ይወዳቸዋል ያከብራቸዋልም ።

አባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ከእናታቸው ማኅፀን እንደ



ሕሙማንን በማጥመቅ ሕንፃ ቤ/ ክርስቲያኑን እንደ አንድ መሐንዲስና እንደ አንድ ወዛደር ሆነው ቤ/ ክርስቲያኑን የሚያገለግሉ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ሕይወት ወ/ ሰንበት አድሐና

ወጡ ወደፈጣሪያቸው ወደ እግዚአብሔር ሦስት ጊዜ ከሰገዱ በኋላ «ከጨለማ ወደ ብርሃን ያወጣኸኝ አምላክ ክብር ምሥጋና ይግባህ» በማለት ገድልን ከአምልኮተ እግዚአብሔር ጋር አዋሕደው የያዙ ታላቅ አባት በመሆናቸው ከልብ ልንወዳቸውና ልናከብራቸው ይገባናል በተለይም ለኛ ለኢትዮጵያውያን ልዩ ፍቅር ያላቸው በመሆን በደብረ ዝቋላ ባሕር ውስጥ ገብተው የኢትዮጵያን ሕዝብ ማርልኝ እያሉ መቶ ዓመት ሙሉ ወደ ፈጣሪያቸው ጸልየው ምህረትና ቸርነት እንዳስገኙልን መጽሐፈ ገድላቸው ይነግረናል ።

እግዚአወሐር አምላክም ለሚወዱት ሁሉ ቅርብ በመሆኑ በጻድቁ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ጸሎት ቁጣውን በትዕግሥት መልሶ ምህረትና ቸርነት መስጠት ልማዱ ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲህ ከባሕሩ ውጣ መላ የኢትዮጵያን ሕዝብም ምሬልሃለሁ ። ኢትዮጵያንም ላንተ አሥራት አድርጌ ሰጥቸሃለሁ ሲል ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል ።

ቃል ኪዳኑም በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከሞቱም በኋላ የሚያማልዱን አባት እንደሆኑ የሚያረጋግጥ ነው። እነሆ ዛሬ በተለያዩ ደዌ ተይዘው በአጋንንትና በመሳሰሉት የሚሰቃዩትን ወደዚህች ቅድስት ቦታቸው እየመጡ ሳይጠራጠሩ የተማፀኑ ሁሉ ካደረባቸው ልዩ ልዩ በሽታ ተፈውሰው ሲሄዱ እናያለን ቅዱስ ጳውሎስ « በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የተገለጸ ነው ለማያምኑግንእይገለጽላቸውም» እንዳለው ሁሉ ከመጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ድረስ በአባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ስም በፈለቀው ፀበላቸው በቡልቡላ ፈለገ ሕይወት ቤ/ክርስቲያን በምሕረቱና በቸርነቱ ተገልጾ ከልዩ ልዩ ደዌአቸው እንዲፈውሳቸው ሽተው የመጡት ሁሉ በምህረቱና በቸርነቱ ፈውሶአቸዋል



በጻድቁ ፀበል በሶፍት የተቋጠረ መድኃኒት ከሆድዋ የወጣላት ምስጋኔ በቀለ ፍንጫ ከተማ ሆሮጉድሩ አውራጃ

የተፈወሱት ሕሙማን በስም ዝርዝር እንደሚከተለው አቅርበናል ።

፩/ አቶ ተስፋ ከበደ አባጨጓሬ መሰል የወጣላቸው ፣ ከአ -አ

፪/ ወ/ሮ ለዓለም መሠረት ከአስም በሽታ የዳኑ ፣ ከአ -አ

፫/ አቶ ብርሃኑ ገ/ሕይወት እባብ መሰል አውሬ የወጣላቸው ከአ -አ

፬/ ወ/ሪት ትዕግሥት ደርቤ እንቁራሪት መሰል የወጣላቸው ከአ-አ

፭/ ወ/ሮ አስናቀች ገ/አምላክ አንድ ቀንድ አውጣ የወጣላቸው ከአ-አ





ከአእምሮ ሕመም የዳነው ተማሪ ብርሃኑ ባለንጎ

፮/ ሲ.ት ሰቦቃ ገብሬ ከአስም በሽታ የዳኑ ፣ ከአ/አ

፯/ አቶ አናንያ ተፈሪ ከጉበት በሽታ የዳኑ ከወለጋ

፰/ ወ/ሮ ምንታምረያቸው ደበሌ አንድ ፀጉር ለበስ አውሬ ፣ ከአ/አ

፱/ ወ/ሮ ምሕረተ.ቃል ፀጋብርሃን ከአስም በሽታ የዳኑ ከአ/አ

፲/ አቶ ገ/ዮሐንስ ገ/ሚካኤል ከአስም በሽታ የዳኑ ከሲዳሞ

፲፩/ አቶ ዳንኤል ዓ/ብርሃን ከጉበት በሽታ የዳኑ ከአ/አ

፲፪/ወ/ሮ ጽርሐ ጽድቅ አንድ ትልቅ ትል የወጣላቸው ከአርሲ

፲፫/ ወ/ሮ አበባ በርሄ አንድ አውሬ የወጣላቸው ከድሬዳዋ

፲፬/ አቶ ተሊላ አንድ ሰው ከአስም በሽታ የዳኑ ከአሰብ

፲፭/ አቶ ይትባረክ ዮሴፍ ከስኳር በሽታ የዳኑ ከጐንደር

፲፮/ ወ/ሮ ጫልቱ ገ/ ማርያም ከአስም በሽታ የዳኑ ከመንዝናግሺ

፲፯/ ወ/ሮ አዛለች ግርማይ አንድ አባ ጓሬ የወጣላቸወ ከአ/አ

፲፰/ አቶ ሐዲስ እንግዳሰው ከጎጃም

፲፱/ አቶ ደምሴ ኀ/መስቀል ከአስም በሽታ የዳኑ ከአ/አ

፳/ አቶ በቀለ ቱፋ አንድ አባ ጨጓሬ የወጣላቸው ከአ/አአ

፳፩/ አቶ በቀለ ቱፋ አንድ አባ ጓሬ የወጣላቸው ከአ/አ

፳፪/ ወ/ሪት ሰብለ ወ/ገብርኤል እባብ መሰል አውሬ የወጣላቸው ከአ/አ

፳፫/ ተማሪ ዳዊት ተክሌ ከስኳር በሽታ የዳነ ከአ/አ

፳፬/ ወ/ሮ ቀለሟ እንግዛሽ አንድ ትልቅ ፀጉር ለበስ አውሬ ከአ/አ

፳፭/ ግርማቸው እንየው ከአስም በሽታ የዳኑ ከባሌ ጉባ

፳፮/ ወ/ሮ ይድነቃቸው ሐዲስ ከጉበት በሽታ የዳኑ ከአ/አ

፳፯/ወሮ ወጋየሁ ኃ/ማርያም ከአስም በሽታ የዳኑ ከአ/አ

፳፰/ ወ/ሮ ወጋየሁ ኃ/ማርያም ከአስም በሽታ የዳኑ ከአ/አ

፳፱/ አቶ አስፋው ጌራሕይወት ከሺባነት የዳኑ ከሐረር

፴/ ወ/ሮ ብታምረያቸው ያሬድ አንድ ጉርጥ የመሰለ አውሬ የወጣላቸው

፴፩/ አያሌው ደመቀ ከአስም በሽታ ከአ/አ

፴፪/ ወ/ሮ ፀሐይነሽ ደምለው ከጉ



በፀበሉ አማካይነት ከሆዷ ውስጥ አውሬ የወጣላት ሕፃን እናኑ ቲመርጋ ።

በት በሽታ የዳኑ ከደብረዘይት

፴፫/ አቶ ሥዩም ገብረሃና ከአስም በሽታ የዳኑ ከአ/አ

፴፬/ ወ/ሮ መዓዛነሽ ደምሴ አንድ ትልቅ አውሬ የወጣላቸው ከናዝሬት

፴፭/ ሕፃን እናኑ መርጋ አንድ እንቁራሪት መሰል አውሬከአ/አ





ጆሮአቸው ደንቁሮ ከዳኑት መካከል

፴፮/ ሕፃን ሄለን ታየ አንድ አባጨጓሬ የወጣላት ከአቃቂ

፴፯/ ወ/ሮ ሙሉጌታ ይርዳው አንድ አውሬ የወጣላቸው ከሐረር ክ/ሀ ከሙለታ አውራጃ

፴፰/ ወ/ሮ መሰለች ዋቅጅራ አንድ አባ ጓሬ መሰል የወጣላቸው ከወለጋ

፴፱/ ተማሪ አብርሃም መለሰ ከአስም በሽታ የዳነ ከሐረር

፵/ አቶ ውብነህ ባያልፈኝ ከአስም በሽታ የዳኑ ከጅማ ክ/ሀ

፵፩/አቶ የሽጉ በጅጋ ቀንድ አውጣ

ከደብረ ዘይት ከፍተኛ፩ ቀበሌ ዜሮ፫ በዚህ አምስት ወራት የተፈወሱት በጥቅል

፩/ ከአስም በሽታ ፫፻፷፰፻፹፪

፪/ ከአጋንንት ልክፍት ፭፻፹፩

፫/ ከነሐቢ እጀ ሰብ ፫፻፲፬

፬/ ከሽባነት ፪፻፰

፭/ ከጨጓራ በሽታ ፫፻፺፮

፮/ ከኩላሊት በሽታ ፺፰

፯/ ከጉበት በሽታ ፹፩

፰/ ከሚጥል በሽታ ፪፻፺፰

፱/ ከልብ ሕመም ፶፪

፲/ አውሬ የወጣላቸው ፩ሺ፪፻፲፫

በጠቅላላው ፫ሺ፬፻፫

ሕሙማን አዲስ አበባ በሚገኘው በቡልቡላ ፈለገ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፀበል የተፈወሱ መሆናቸውን በዛሬው ዕለት በአባታችን በዓል ስም ለተሰበሰባችሁ ምእመናን ስገልጽ በታላቅ ትሕትና ነው ሲሉ የደብሩ አስተዳ

www.ethiopianorthodox.org

ዳሪ መልእከ ሕይወት ወልደ ሰን በትእድሐና መገሌጫቸውን ደም ድመዋል ። ይህ የፈለገ ሕይወት ቡልቡላ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤ/ክርስቲያኑ ከተተከለ አጭር ጊዜ ቢሆንም በእግዚአብሔር አምነው

በጸድቁ ተማጽነው በፀበሉ ተጠ ምቀው የዳኑ ሕሙማን እጅግ በር ከት ያሉ ናቸው ። ስለዚህ አሁንም ወደፊትም ይህ የዝግጅት ክፍሉ በጸድቁ ስም የፈለቀው ተአምራዊ

ፀበል የማያቋርጥ ፈውስ ስለሚ ሰጥ የታመሙ ወገኖች ሁሉ ወደ ዚህ ሥፍራ እየኼዱ እንዲፈወሱ መንፈሳዊ መልእክታችንን እናስ ተላልፋለን ።

## በብሪታንያ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሥራ ፍሬ

የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ የ፲፱፻፹፭ ዓ/ም የል ደት በዓል በብሪታንያ በምትገ ኘው የቅድስት ድንግል ማርያም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በደማቅ ሁኔታ መከበሩን ክቦታው ዘግይቶ የደረሰን ዜና ገለጸ ።

በዚሁ በዓል ላይ የብፁዕ ወቅ ዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልእክት ለምእመናን በንባብ ስለ ተሰማ የምእመናኑ ደስታ እጅግ ከፍተኛ እንደነበረ ታውቋል ።

የዕለቱ ጸሎተ ቅዳሴ በሊቀ ብር ሃናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ መሪነት ከሌ ሊቱ ስድስት ሰዓት እንደ ኢ. አቈጣጠር እንደብሪታንያ አቈጣ ጠር በ፲፪ሰዓት ተጀምሮ በ፰ ሰዓት ተኩል ተፈጽሟል ።

በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ የተገኙ እንግዶችና ምእመናን በቤተ ክር ስቲያኑ የስብሰባ አዳራሽ ተገኝ ተው ታላቅ ግብዣ ተደርጎላቸዋል እንዲሁም በዚሁ የበዐለ ገና ዕለት እኩለቀን ላይ በአቶ ማኅተመ ሥላሴ ስቲቫንስ ቤት ካህናትና ምእመናን ወጣቶች ባደረጉት እስ ተዋጽኦ ጭምር የተዘጋጀ ታላቅ የምሣ ግብዣ ተደርጎአል ።



ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ ከካንተርቨሪው ሊቀ ጳጳስ ጋር ።

ከግብዣው ፍጻሜ በኋላ ሰበካ ጉባኤው ያዘጋጃቸው ልዩ ልዩ የል ደት ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ በሊቀ ብርሃናት ሰሎ ሞን ገብረ ሥላሴ እጅ ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተሰ ጥቶ እንዳበቃ አስተዳዳሪው ለም እመናኑና ለሰበካ ጉባኤው የሚያ በረታታ መንፈሳዊ ንግግር ከማድ

የዕለተ ልደት አከባበር ካረቢ ያንና ኢትዮጵያውያን ምእመናን በተገኙበት ጸሎተ ኪዳን ደርሶ እንዳበቃ የልደትን በዓል የሚመ ለከቱ ወረቦች ተወርበዋል ። ሽብ ሸባው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን ሥርዓትና ወግ መሠረት በጸናጽልና በከበሮ ስለነበረ ከበር ሙኾበት ፤ ጸናጽል ተንሻሾቶበት ፤ ለማያውቅ ምድረ አውሮፓ ታላቅ ድምቀት ሰጥቶት እንደነበረ ከደ ረሰን ዜና ለመረዳት ችለናል ።

በለንደን ቅ/ ማርያም ቤ/ ክርስቲያን የልደት በዓል አከባበር ።





በጌታችን በዓለ ልደት ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ከሕፃናት ጋር ሲያከብሩ ።

ረጋቸውም በላይ ምስጋና አቅር በዋል ።

**፪/ ጥምቀት ፤**

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ የ፲፱፻፹፭ ዓ/ም በዐለ ጥምቀት በብሪታንያ ተከ ብሮ የዋለ መሆኑን ከብሪታንያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ ተ ክርስቲያን ዘግይቶ የደረሰን ዜና አስረዳ ።

በሪፖርቱ እንደተገለጸው የጥ ምቀት በዓል በብሪታንያ ሲከበር የመጀመሪያ በመሆኑ ጊዜያዊና ዘ መናዊ ተከትሮ እንደኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር ዓት ጸሎተ ወንጌል ደርሶ ጸበሉ በአስተዳዳሪው ተባርኮ ለም እመናን ተረጭቶአል ።

ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ በብሪታ ንያ የታየው ሥርዓተ ጥምቀት ካራ ቢያኑን እጅግ አድርጎ ያስደሰታ ቸው መሆኑ በዜናው ተገልጾአል ።

**፫/በዓለ አስተርዮ**

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ ዕረፍት (አስተርዮ ማርያም) በለንደን ከተማ ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ/ም በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ መዋሉ ከዚሁ ሪፖርት ጋር ተገልጾአል ። በዚሁ በዓል ላይ ምእመናን በብዛት የተገኙ ሲሆን ወ/ሮ እኔት ቶኒ የተባሉት ምእመን ፤ ፩ኛ ክርስቶፎር ድዋኒ ፤ ፪ኛ ዊልያምስ ኩዮሪን የተባሉ ልጆቻቸው ክርስና እንዲነሡላቸው አቅርበው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ተጠምቀው ስመ ጥም ቀታቸው «ፍቅርተ ማርያም፡በዕደ ማርያም» ተብሎ መሰየሙ ተገልጾ እንደ ቤተክርስቲያን ሥርዓትየበዓለ ክርስትናው ግብዣ በእማንያኑ ቤት ተከናውኗል ።

በዚሁ ዕለት በጻድቃንና ሰማ ዕታት ስም ማኅበር እንዲቋቋም ተደርጎ በየወሩ ዝክር ለመዘከር ተስማምተዋል ።

ለዚሁ ማኅበር በጎ አድራጊዎች ከሁለት ፓውንድ እስከሁለት መቶ ፓውንድ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ታውቋል ።

**፬ ፤ ዐቢይ ጾም ።**

በማዕከለ አውሮፓ ጾም ብዙም ያልተለመደ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን እምነትና ሥርዓት በሚፈቅ ደው መሠረት የዐቢይ ጾምን ምእ መናኑ ጾመዋል ።

በየሳምንቱ ዐርብ በሚደረገው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ስለጾ ም ጠቃሚነት በመደጋገም በቂ ትምህርት የተሰጠ በመሆኑ በን ስሐ አባቶቻቸው አማካይነት ስለ ጾም አስፈላጊነት እየተረዱ መዋ ዕለ ጾሙን ጾመዋል ።

**፭ የጸሎተ ሐሙስ ፤**

እንዲሁም የሆሳዕናና የስቅለት የትንሣኤ በዓላትም እንደ ኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥር



www.ethiopianorthodox.org

ዓት በታላቅ ድምቀት ተከብሮ መዋሉን ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ የቤተ ክርስቲያኑዋ ኃላፊ ከላኩት ቤፊ ሪፖርት ለመ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ቁጥር እየጨመረናእድገት እያሳየ መሆኑን ገልጸው ። ለዚህም የሰበካ ጉባኤ

ፍ ለማሳተም በዝግጅት ላይ እን ደሚገኙና በሀገሪቱ የሬድዮና ቴሌ ቢዥን ቤተ ክርስቲያኑዋን/ለማስ



በለንደን ቅ/ ማርያም ቤ/ ክርስቲያን ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ ሥላሴ የኢትዮጵያን ሬዲል ከሚያስተም ሩአቸው ሕፃናት በከፊል ።

ረዳት ተችሎአል፡ በመጨረሻም ስ ለ ወደፊቱ የሥራ ዝርዝር እንደ ገለጹት ፤

ምዝገባ በጥራት እንዲካሄድ ቅድ ስት ቤተ ክርስቲያናችንን በይበ ልጥ ለማስተዋወቅ የሚረዳ ጽሑ

ተዋወቅ ዝግጅት እየተደረገ መሆ ኑን አብራርተዋል ።

ተስፋ ጥሩነህ



በለንደን ቤ/ ክርስቲያናችን የሰንበት ት/ ቤት ሕፃናትና ወላጆች በከፊል ።

# ስብከተ ወንጌል በልማት ተግባር

ሬታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮም የምት ሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ» ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ስላዘዛቸው ይህ ንኑ የጌታ ቃል በተግባር ለመተር ጐም ከከተማ ወደ ገጠር ወደ ባላገር ሲሄዱ«እንደ እባብ ልባሞች እንደርግብ የዋሆች ሁኑ» የሚለው ን መመሪያ በመከተል ነው በዚ ሁም መሠረት በቅድሚያ ቅዱስ ወንጌልን ለሕዝቡ በማስተማር ሕ ሙማንን በጌታ ስም በመዳሰስና በመፈወስ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽና በማቋቋም ተልእኮአቸ ውን በተግባር አሳይተዋል ።

ይህ ሁሉ የአንድ ሰባኬ ወን ጌል ግዴታዊና ውዴታዊ ተግባሩ ነው ዛሬም ቢሆን ለወንጌል አገል ግሎት የተጠሩ (የተመረጡ) መም ህራን የአባቶቻቸውን አሠረ ምግ ባር ተከትለው ሐዋርያዊ ግዳጃቸ ውን በተግባር ተርጉመው በማሳ የት ላይ የሚገኙ ጥቂቶች አይ ደሉም ።

ከነዚህም መካከል በምሥራቅ ሐረርጌ የወበራ አውራጃ ሊቀ ካህ ናት ሰባኬ ወንጌል ሊቀ ትጉሃን ይትባረክ ታጠቅ ይገኙባቸዋል ፣ ሊቀ ትጉሃን ይትባረክ ታጠቅ በ፲፱ ፻፸፩ ዓ/ም በሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በስብከተ ወንጌል ሥራ ተመድበው ወደ ወበራ አውራጃ ከተላኩበት ጊዜ ጀምሮ በየቦታው እየተዘዋወሩ ቃለ ወንጌል ለሕዝበ ክርስቲያኑ በማስተማር ለአንድ ዓ መት ከቆዩ በኋላ የአውራጃው ቤ/ክ ህነት ሥራ አስኪያጅነት ደርበው እንዲሠሩ ከሀ/ስብከቱ ጽ/ቤት ደብ ዳቤ እንደ ተጻፈላቸው የግል ማኅ ደራቸው ይጠቁማል ።

ከዚህ በፊት በአውራጃው በስ ብከተ ወንጌል ትምህርትና በመንፈ ሳዊ አገልግሎት ረገድ የተዳከመ እንደ ነበረና በሰበካ ጉባኤና በሰን በት ት/ቤትም በኩል የተሟላ እን ዳልነበረ በጊዜው ሲደረግ ከነበረ ው የአጻጻፍ ለውጥ መረዳት ይቻ ላል ።

ሊቀ ትጉሃን ይትባረክ ወደዚሁ አውራጃ ከተዛወሩበት ዓመተ ምህ ረት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በስብ ከተ ወንጌልና በመንፈሳዊ አገልግ ሎት በሰበካ ጉባኤ መቋቋም በሰን በት ት/ቤት አደረጃጀትና በልማት ተግባራት ያደረጉት የሥራ እንቅ ስቃሴ እንዳለ ማዕዶት ላቀረበላ ቸው ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ ፣



ሰባኬ ወንጌሉ ሊቀ ትጉሃን ይትባረክ ታጠቅ እኒህ ናቸው

እኔ ወደ አውራጃው እንደተዛወ ርሁ የሥራዬ መጀመሪያ ያደረግ ሁት የምእመናንን ልቦና በስብ ከተ ወንጌል ትምህርት ማነጽ ነው ይኸውም በገጠርና በከተማ የሚ ገኙት ክርስቲያኖችን በየአብያተ ክርስቲያናቱ በየክብረ በዓላቱ በየ ዕድሩ እየተገኘሁ የማኅበራዊ ኑሮ ትምህርትና ቃለ ወንጌልንም በመ ስጠት ምእመናን ክርስቲያናዊ ሕይ ወታቸውን እንዲያጠነክሩና ለበጎ ዓላማም እንዲሰለፉ አድርጌአለሁ ። ምእመናኑ በጥንቃቄ መያዙ አስ ፈላጊ ስለሆነ ካህናት የንስሐ ልጆ ቻቸውን በቅድሚያ እንዲያስመ ዘግቡ በሰጠሁት መመሪያ መሠረት ባሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ታውቆ ስማ ቸው በመመዝገቢያ ፎርም ተሞ ልቶ አስተዋጽአውንም ወቅቱን እየ ጠበቁ እንዲከፍሉ በመቻላቸው ሰ በካ ጉባኤን በጠነከረና በሠመረ ሁኔታ ለማቋቋም ችያለሁ ስለዚህም ባሁኑ ጊዜ በአውራጃው ያሉት አብ ያተ ክርስቲያናት በሰበካ ጉባኤ ተደራጅተውና ተጠናክረው ይገኛ ሉ ብለዋል ።

ንግግራቸውንም በመቀጠል ሥራ ክቡር እንደመሆኑ መጠን የሥራ ውጤትም የሚለካው በፍሬው ስለ ሆነ ከላይ ከተጠቀሰው ዓመተ ምህረት ጀምሮ በደደር ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በጎ አድራጊዎችን በማስተማር ለሰንበት ት/ቤት ለእንግዶች ማረፊያ ፣ ለመንፈሳዊ ት/ቤት የሚያገለግሉ ቤቶችን አሠርቻለሁ። የደደር ደብረ ሲና ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን መብራት ስላልነበረው አንድ በጎ አድራጊ ምእመን ፣ ኤሌ ክትሪክ መብራት እንዲያስገቡ ለት ስላሳሰብኳቸው ባሁኑ ጊዜ ቤ/ክርስቲያኑ በኒሁ በጎ አድራጊ ሰው አማካይነት መብራት ገብ ቶለት የተሟላ መንፈሳዊ አገል ግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል መብራቱ የቈጠረው ገንዘብ አንድ በጎ አድራጊ እንዲከፍሉ ስለ እሳ ሰብኳቸው በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ያድላቸውና በየወሩ ገንዘ ቡን በመክፈል ላይ ይገኛሉ ።

በዚህች በደደር ደብረ ሲና ቅ/ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት አቋቁሜ ከማደራጀቴም በ ላይ በተለይ የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልጋዮች የሚሆኑ ዲያቆናት አስተምሬ መዓርገ ዲቁናንም አሰ ጥቼ ባሁኑ ጊዜ በመንፈሳዊ አገል ግሎት ላይ ይገኛሉ ካሉ በኋላ የጥ ያቄውን መልስ በማራዘም ሲያብ ራሩ በዚሁ አካባቢ የሚገኘው የደ ደር ገነተ ልዑል ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከተሠራ ብዙ ዘመናት ያሳለፈ ስለሆነ ግንቡ ተሰነጣጥቆና ጣራው ተንቃቅሎ ሊፈርስ ተቃ ርቦ ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህም ጉዳይ አሳሳቢ ሆኖ ስላገኙት የአሠሪ ኮሚቴ በሰበካ ጉባኤ አማካይነት ካቋቋሙኹ በኋላ ኮሚቴው ሥራውን በፍጥነት ጀምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቤ/ክርስቲያኑ በጠንከረ ሁኔታ ተጠግኖ ሙሉ እድሳት ተደርጎለታል እንዲሁም የደሩ መድሎተ አሚን ኪዳነ ምሕረት ጽላት ለ፳፯ ዓመታት ያህል በመቃኞ ከኖረች በኋላ የሰበካው ምእመናንና የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን በማስተባበር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አሠርቸ ታቦቷ ወደ ዋናው ቤ/ክርስቲያን እንድትገባ አድርጌአለሁ ሲሉ አስረድተውናል ።

የወበራ አውራጃ ሊቀ ካህናት ሊ/ትጉሃን ይትባረክ ታጠቅ ከዚህ ሌላ ተጨማሪየተሠራ የልማት ሥራ እንዳለ እንዲገልጹልን ላቀረብንላቸው መጠይቅ ሲያብራሩ በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል በነበረው ግጭት ምክንያት በዚሁ አውራጃ በደደር ወረዳ የሶቃ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ስለተደመሰሰ ባሁኑ ጊዜ የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ይሠራልን ብለው ጥያቄ በማቅረባቸው ፣ በምእመናኑ ጥያቄ መሠረት ሕዝቡን አስተባብሬና አስተምሬ ከፍተኛ ገቢ ተገኝቶ በተገኘው ገንዘብ ቤተ ክርስቲያኑን በዘመናዊአቅድ አሠርቶናል በተጨማሪም ቤተ ልሔምም በጥሩ ሁኔታ እንዲሠራ ተደርጎ ባሁኑ ወቅት ታቦተ ሕጉ ወደ መንበረ ክብሩ ገብቶ መንፈሳዊ አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ይገኛል ።

እንዲሁም በዚሁ ወረዳ የቆቦ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ከተሠራ ብዙ ዘመናት ያሳለፈ በመሆኑ እድሳት እንዲደረግለት ወስነን በጎ አድራጊ የሆኑ ግለሰቦችን በማስተባበርና ሰበካ ጉባኤንም በማቋቋም ካጠናከርን በኋላ ሙሉ እድሳት እንዲያገኝ አድርገናል ከዚህ በላይ ለሃይማኖታቸው ቀና እያን የሆኑ ትንና እምነታቸውንም በተግባር ለመግለጽ የፈለጉትን ምእመናን አስተባብሬ አራት ሰዎች አንዱ መንበር አሠርቶአል ፤ ሁለተኛው ኤሌክትሪክ መብራት ፣ ሦስተኛው የውኃ ቧንቧ፣ አራተኛው ድምጽ ማጉያ አስገብተዋል ከዚህም በላይ የተሟላ ንዋያተ ቅድሳት አስገዝቼ የተሟላ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጌአለሁ ።

በተጨማሪም የጎረ ጉቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሶማሊያ ወራሪ ወንበዴዎች ጉዳት ስለደረሰበት ጽላቱ ከቤተ መቅደሱ ወጥቶ በካራ ሚሌ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ለ፲፩ ዓመታት ያህል ቆይቶአል ስለዚህ አሁን ምእመናኑ ቤ/ክርስቲያናችን ይታደስልንና ታቦቱም ተመልሶ ወደ መንበሩ ይግባልን ብለው ስለጠየቁን ጥያቄአቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በየጊዜው ከቦታው እየተገኘሁ መመሪያና ትምህርት እየሰጠሁ ስላነቃቃኋቸው ምእመናኑ ከፍያለ የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርገው ቤ/ክርስቲያኑ የጠመመውን ተቃንቶ የጎደለውን ተሟልቶ ሙሉ ዕድሳት አግኝቶ ከተፈጸመ በኋላ ታቦቱ ገብቶ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ቀጥሎአል ።

ከዚህም ጋር የበረዳ ቅ/ጊዮርጊስ ቤ/ ክርስቲያን በዘመናትብዛትግንቡ ተሰነጣጥቆ ጣራው ተገነጣጥሎ ሲፈርስ ተቃርቦ ስለተመለከትሁ በሐዋርያዊ ግዴታዬ መጠን ሕዝቡን በማስተባበርና ቀስቃሽ ትምህርትም በመስጠት ገንዘብ እንዲዋጣ ካደረግሁ በኋላ ሙሉ እድሳት እንዲያገኝ ቤ/መቅደሱና ቅኔ ማኅሌቱም በሲሚንቶ እንዲሠራ ዙሪያው በአጥር እንዲከበርና ባለው ክልል ውስጥ ከ፲፱ ሺህ ያላነሰ ባሕርዛፍ እንዲተከል አስደርጌአለሁ ።

ከዚህም ሌላ የካራሚሌ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ አንድ በጎ አድራጊ ምእመን ሙሉ እድሳት እንዲያደርጉለት ቃል የገቡ ሲሆን እንዲሁም በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ክልል ከአሥር ሺህ ያላነሰ ባሕር ዛፍ አስተክዬ ባሁኑ ጊዜ ለሽያጭ ደርሶ ይገኛል ከዚህም በላይ አልባሳቱና ንዋያተ ቅድሳቱ እንዲሟላ ያደርጉ ዘንድ ለምእመናኑ በሰጡት ትምህርትና መመሪያ መሠረት አንድም ሳይቀር ሁሉም ተሟልቶ በሥራ ላይ ውሎአል ።

ሌላው ባሁኑ ጊዜ የጨለንቆ በዓለ ወልድ ጽላት በመቃኞ ይገኛል ስለሆነም ሕዝበ ክርስቲያኑ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ለማሠራት ስላቀደ እኔም ሕዝቡን በማስተማርና በማስተባበር ቀስቃሽ ትምህርትም በመስጠት ባደረግሁት ጥረት ሥራው በእግዚአብሔር ቸርነት ተሳክቶልኝ ማስተር ፕላኑ ወጥቶ ሕንፃውን ለመጀመር ቅድመ ዝግጅቱን በተሟላ ሁኔታ ተከናውኖ ይገኛል ።

በአጠቃላይ በዚህ አውራጃ በእያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያናት የባሕር ዛፍ ችግኝ እንዲተከል በሰጠሁት የሥራ መመሪያ መሠረት ከሰባ ሺህ በላይ የሚሆን ባሕር ዛፍ ተተክሎ ባሁኑ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ይገኛል ።

በ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በሀገራችን ድርቅ ባስከተለው ጠንቅ የተከሰተው ረሀብ በደደር ወረዳ ብዙ ሕዝብ በችግር ላይ ወድቆ ነበር በዚያው ወቅት እኔ ለሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ለብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የችግሩን አስከፊነት በጽሑፍአመልክትሁ ብፁዕነታቸውም ማሳሰቢያዬን በመቀበል ጉዳዩን ከሚመለከታቸው ጋር እነጋገርበታለሁ በማለት ተስፋ ከሰጡኝ በኋላ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ጋር ተነጋግረው ወደ ቦታው ሄዶ የሚያጠና ቡድንተላከ

ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ቡድኑ በመጣ ጊዜ ወደኔ ስለላኩት ከኔ ጋር ሆኖ ችግሩን መርምሮ ካጠና በኋላ ከሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች ጋር ተነጋግሮ የርዳታ ጣቢያ መቋቋም እንዳለበት አምኖ አጸደቀ ። ስለዚህ ፩ኛ/ በደደር ፣ ፪ኛ/ በሐረዋጫ ጣቢያዎች ተቋቋሙ በእነዚህ ጣቢያዎች ቤ/ክርስቲያን የወገንና የሃይማኖት ልዩ ነት ሳታደርግ ፣ ለሁለት ዓመታት ያህል የምግብና የልብስ የቁሳቁስና የሕክምና ርዳታ ስትሰጥ ቆይታለች ፣

በዚሁ ርዳታ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሕይወታቸው ሊተርፍ ችሎአል የሀገራችን ተፈጥሮ ወደ ነበረው ጸጋ ተመልሶ ሕዝቡም በምርቱ መጠቀም ከጀመረ ወዲህም ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የሀ/ ስብከቱ ሊ/ጳጳስ ከልማት መምሪያው ጋር በመነጋገር በቦታው ፕሮጀክት እንዲቋቋምና ቀደም ብሎ በርዳታው ይተዳደሩ የነበሩት አርሶ አደር ገበሬዎች ራሳቸውን እንዲችሉና ከተረጅነት ወጥተው አምራች ዜጋ እንዲሆኑ በማሳሰብ በአውራጃ ፕሮጀክት እንዲቋቋም ተደርጎአል ። ይኸው ፕሮጀክት ለሁለት ሺህ ሁለት መቶ ገበሬዎች የእርሻ በሬዎችን አድሏል እንዲሁም ምርጥ ዘርና የእርሻ መሣሪያዎችን ሰጥቷል ።

ከነዚህም ውስጥ ለአርሶ አደሩና ከሥራው ጋር ግንኙነት ላላቸው የቤ/ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት በሬ ምርጥ ዘርና የእርሻ መሣሪያ እንዲሰጣቸ በመደረጉ ባሁኑ ጊዜ በግልም ሆነ በኅብረት እያረሱ ራሳቸውንና ቤተ ሰዎቻቸውን በመርዳት ላይ ይገኛሉ ።

ባሁኑም ወቅት ቢሆን የአውራጃው መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት በገጠር ለሚገኙት አርሶ አደር ገበሬዎች የጉድጓድ ውኃ በመቆፈርና ምንጭ ውኃዎችን በማጐልበት ፣ ቧንቧ በመዘርጋት ላይ የሚገኝ ሲሆን በአውራጃችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የሆነ መንፈሳዊና የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎትን በመስጠትዋ ወገናዊነትዋና ጥንታዊነትዋን አስመስክራለች ፣በመሆኑም ይህ ሁሉ የብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የሐረርጌ ሀ/ ስብከት ሊቀ ጳጳስ መልካም አመራርና የልማት መምሪያውም ዕቅድ ሲሆን እኔም በበኩሌ ይህንኑ ተግባራዊ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቻለሁ ። አሁንም ለወደፊቱም ሥራው ተግባራዊነት እንዲኖረው በተጣለብኝ አደራ መሠረት በየሥራ መስኩ ሁሉ ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ አልቆጠብም ለሁሉም ኃይል ፣ ጥበብ ፣ ትዕግሥትና ታማኝነትን ሁሉ የሚሰጥ አምላክ እንዲረዳኝ የዘወትር ጸሎቴ ነው ሲሉ ሊቀ ትጉሃን ይትባረክ ታጠቅ በምሥራቅ ሐረርጌ አስተዳደር ሀ/ ስብከት የወበራ አውራጃ ሊቀ ካህናት ማዕዶት ያቀረበላቸውን ቃለ መጠይቅ ሐተታዊ መልሳቸውን ደምድመዋል ።

የማዕዶት መጽሔት ዝግጅት ክፍል





www.ethiopianorthodox.org

## የአቶ ኃይሉ መላኩ አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ ኃይሉ መላኩ በጐንደር ክፍለ ሀገር በሰሜን አውራጃ በጃ ናምራ ወረዳ ልዩ ስሟ ደረስጌ ማርያም በተባለችው ክርእሰ ደብር መላኩ ዓለምና ክወይዘሮ ሐበሻ በለጠ በ፲፱፻፳፮ ዓ/ም ተወለዱ ።

ዕድሜአቸው ለትምሀርት እንደ ደረሰ በዚሁ ደብር መንፈሳዊ ትም ሀርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተው ሥርዓተ ቅዳሴን ጠንቅቀው ስላ ወቁ የዲቁና ማዕረግ ተቀብለው መንፈሳዊ ተልእኮአቸውን በመቀ ጠል እባትና እናታቸውን በሥራ ሲረዱ ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በንግድ ሥራ ላይ ተሰማሩ ።

አቶ ኃይሉ መላኩ በጋብቻ ዓለም ውስጥ መንፈሳዊውን ተግባር ተከ ትለው የቆዩ ታላቅ የቤተሰብ መሠ ረት ሲሆኑ ከባለቤታቸው ከወይ ዘሮ መዓዛ ሉዛ ስምንት ልጆች አፍርተዋል ።

አቶ ኃይሉ መላኩ ከአብራካ ቸው ያተከፈሉ ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን መላ ዘመዶቻቸውን ሁሉ በመቀበል እያሰባሰቡ ሲያስተምሩ፣ ሥራ ሲያሲዙና ራሱን ሲያስችሉ የኖሩ የብዙ ሰዎች ባለውለታ ናቸው

አቶ ኃይሉ በሕይወት ዘመና ቸው ውስጥ የአካባቢው ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ያቀረ በውን ሀሳብ በመደገፍ የቤተ ክርስ ቲያኑ እሠሪ ኮሚቴ አባል በመ ሆን በአላቸው ጽኑ የሃይማኖትና የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ከጓደኞቻ ቸው ጋር መቃኞ በማሠራት አሁን ቤተልሔም ሆና የሚያገለግለውን የሰሜን ተራራ ደብረሲና ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ታቦተ ሕግ



አቶ ኃይሉ መልአኩ እኚህ ነበሩ

ሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ/ም እን ዲገባ አድርገዋል ።

ከዚያም የቤተ ክርስቲያኑ እሠሪ ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ በመሆን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ተሠርቶ ታቦተ ሕጉ እስከገባበት ድረስ አገልግለዋል ።

አቶ ኃይሉ መላኩ ለቤተ ክርስ ቲያኑ የሚያስፈልጉትንም የኤሌክ ትሪክ መብራት፣ የተሟላ የውኃ አገ ልግሎት እንዲያገኝ ልዩ ልዩ አድር ገዋልመጻሕፍትን በመግዛትና ሁለት ስንክሳር በብራና አጽፈው ለአም ስት ልኡካን ልብሰ ተክህኖና ለአ ሥራ ሁለት መዘምራን ጥንግ ድርብ በስተምዕራብ በኩል ለታቦት ማቆ ሚያ የሚያገለግል ሞዛይክና በስተ ደቡብ በኩል ያለውን የብረት መዝ ጊያ የቅዱስ መርቆሬዎስን ፣ የእ መቤታችንንና የቅዱስ እግዚአብ ሔር አብ ሥዕሎችን በግል ገንዘ ባቸው አሠርተው አበርክተዋል ፣

አቶ ኃይሉ መላኩ በዚሁ ደብር በከፍተኛ የሕዝብ ድምፅ ተመር ጠው ከ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ጀምሮ እስከ አረፉበት ጊዜ ድረስ የሰበካ ጉባዔ ምክትል ሊቀ መንበር ሆነው ሲያ ገለግሉ ቆይተዋል ።

አቶ ኃይሉ መላኩ ደከመኝ ሰለ ቸኝ ሳይሉ መላ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን ለሰሜን ተራራ ደብረ ሲና ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ሥራ አውለዋል ።

ከዚህም ሌላ ለትውልድ ሀገራ ቸው ለጽርሐ ጽዮን ቅድስት ደረ ስጌ ማርያም ደብር ቤተ ልሔምና ሁለት ደጀ ሰላም ክዳኑን በቆርቆሮ አስለብሰዋል ። ለማስቀደሻ እንዲ ውል ሙሉ አልባሳትና አንድ ላንታ ካባ እንዲሁም አንድ ቋሚ የግድ ግዳ ሰዓት ፣ በየዓመቱ ለማስቀደሻና ለማስወደሻ የሚሆኑ መገልገያዎ ችን ከማበርከታቸውም በላይ በሰ ሜን አውራጃ ለደባርቅ ከተማ የመ ብራት አገልግሎት ለኅብረተሰቡእን ዲዳረስ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸ ውን አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እም ላክ ሥጋ ለለበሰ ሁሉ የሰጠው የማ ይዛባ የሞት ፍርድ እርሳቸውም ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም በተወለዱ በ፶፫ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። ሆኖም በጎ ምግባራቸው ዘወትር ከእኛ ጋር ስለሚኖር እንጽናናለን።

ባለቤታቸው ወ/ሮ መዓዛ ሉዛና

ቤተ ሰቦቻቸው



## የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ፩ኛ ዓመት በዓለ ሢመት አከባበር የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ









www.ethiopianorthodox.org